የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፵
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No.40
ADDIS ABABA 2nd May, 2025

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፬/፪ሺ፲፯
የንብረት ማስመለስ አዋጅ .....ገጽ ፲፰ሺ፫፻፳፩

Content

Proclamation No. 1364/2025
Asset Recovery Proclamation .....Page 18321

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፬/፪ሺ፲፯
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንብረት ማስመለስ አዋጅ

የኢኮኖሚ ወንጀል በሃገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ በመሆኑ ይህንን ወንጀል መከላከል እና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ እና ማንኛውም ሰው ከሕገ-ወጥ ድርጊት ማንኛውንም ዓይነት የኢኮኖሚ ጥቅም ማግኘት እንዳይችል የሚያደርግ ሥርዓት በሕግ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በወንጀል የተገኘ ንብረትን ማጥናት፣ መለየት፣ ማገድ፣ መያዝ፣ መመርመር፣ መክሰስ፣ ንብረት ማስተዳደር እና መውረስን የሚመለከቱ በተለያዩ ሕጎች ተበታትነው የሚገኙ ድንጋጌዎች በአንድ የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ በማምጣት እና ለሁሉም የወንጀል ዓይነቶች እንዲያገለግሉ በማድረግ ለመሠረታዊ የሕግና የአፈፃፀም ጥያቄዎች ወጥነት ያለውና በቂ መልስ የሚሰጥ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ምንጩ ያልታወቀ ንብረት በሃገሪቱ የግብር ሥርዓት፣ የውጭ ምንዛሬ፣ የገንዘብ ዝውውር ሥርዓት እና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ በመሆኑ እና ያለው የሕግ ማዕቀፍ በመንግስት እና በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኞች ላይ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ችግሩን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

PROCLAMATION NO. 1364/2025
ASSET RECOVERY PROCLAMATION

WHEREAS, no one shall obtain any kind of benefit from an illegal act and it becomes necessary to etablsih a legal framework that prevents and suppres the detrimental effect of the economic crimes on the economy of the country;

WHEREAS, it is essential to ensure for the promulgation of comprhensive asset recovery laws for all kinds of crimes generating proceed that covers asset identification, investigation, freezing, seizure, confiscation and asset management as the existing laws outlined in different proclamations lack sufficient provisions to adequately address the fundamental legal and practical issues;

WHEREAS, it becomes necessary to issue the law as unexplained asset has a negative impact on the country's tax system, forign currency, financial flow, forign direct investment and the existing legal framework lacks the possibility of preventing and suppressing unexplained wealth as the applicability is only limited to public servants and public organization employees;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 1868.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ኢትዮጵያ በወንጀል የተገኘ ንብረት ማስመለስን በተመለከተ ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በተግባር ለማስፈፀም እና በወንጀል ድርጊት የሚገኝ ንብረትን ማስመለስ፣ መውረስና ማስተዳደርን በተመለከተ ዓለም አቀፍ መለኪያዎችን የሚያሟላ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የንብረት ማስመለስ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፷፩/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ንብረት" ማለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ፣ የማይንቀሳቀስ፣ ገንዘብ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ሀብት ሲሆን በሀብቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም መኖሩን የሚያረጋግጥ እንደ ባንክ ክሬዲት፣ ትራቭለር ቼክ፣ የባንክ ቼክ፣ የክፍያ ትዕዛዝ፣ ምናባዊ ንብረት፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ አክሲዮን ወይም ቦንድ የመሰለ ማንኛውንም ዓይነት ሰነድ እና ከሀብቱ የተገኘን ወለድ፣ የትርፍ ድርሻ ወይም ሌላ ገቢን ወይም ማናቸውንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ይጨምራል፤

፪/ "የወንጀል ፍሬ" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከወንጀል ድርጊት የተገኘ ማንኛውም ንብረት ሲሆን ይህንኑ ንብረት መሠረት አድርጎ የተገኘ ገቢ ወይም ትርፍ፣ ለወንጀል መፈፀሚያነት ከዋለ ንብረት የሚገኝ ገቢ ወይም ትርፍን ይጨምራል፤

፫/ "የወንጀል መፈጸሚያ" ማለት በማንኛውም መንገድ በሙሉ ወይም በከፊል ለወንጀል ድርጊት መፈፀሚያነት የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ ንብረት ነው፤

WHEREAS, it is necessary to establish a legal framework that not only aligns with the standards set forth in international agreements ratified by Ethiopia on asset recovery and management but also facilitates the practical implementation of these standards;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Asset Recovery Proclamation No. 1364/2025."

2. Definitions

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ **"Asset"** means any movable, immovable, money, tangible or intangible assets including legal instruments in any form evidencing title to or interest in such assets such as bank credits, traveler's cheques, bank cheques, money orders, vertual asset, securities, shares or bonds or any other document similar to that and includes, interest, dividend or other income or value generated by such asset;

2/ **"Proceeds of crime"** means asset directly or indirectly obtained from a crime and it includes income or profits from the proceeds or the instrumentality of a crime;

3/ **"Instrumentality of a crime"** means any asset used or intended to be used in any manner, wholly or in part, to commit any offense;

፬/ "ተጎጂ" ማለት በወንጀሉ ምንም ተሳትፎ ሳይኖረው በተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ምክንያት ንብረቱን፣ በንብረቱ ላይ ያለውን መብት ወይም ጥቅም ያጣ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው ነው፤

4/ **"Victim"** means a person who loses an asset, a right or benefit on such asset, or suffers economic damage due to a crime committed, without having any participation in the crime;

፭/ "ንብረት ማስመለስ" ማለት የወንጀል ፍሬ የሆነ ንብረት፣ ከወንጀሉ ፍሬ ተቀላቅሎ ወይም ተለውጦ የተገኘ ንብረት፣ ከወንጀሉ ፍሬ የተገኘ ገቢና ሌሎች ጥቅሞችን የሚመለከት ንብረት፣ ለወንጀሉ መፈፀሚያነት የዋለ ንብረት ወይም ከዚህ ንብረት የተገኘ ገቢ ወይም ትርፍ፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን ማጥናት፣ መለየት፣ ማገድ፣ መያዝ፣ መመርመር፣ በንብረት አስተዳዳሪ ስር ማቆየትና እንዲወረስ ማድረግ ነው፤

5/ **"Asset Recovery"** means survey, identification, tracing, freezing, seizure, investigation, asset management and confiscation of assets constituting the proceeds of the crime, intermingled with or exchanged assets for such proceeds, any income or other benefits obtained from the proceeds of the crime, instrumentalities of a crime or any income or profit thereof or unexplained asset;

፮/ "መውረስ" ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የንብረት ባለቤትነት መብትን በዘላቂነት ማሳጣት ነው፤

6/ **"Confiscation"** means the permanent deprivation of ownership rights upon the asset based on the decision of the court or any authority authorized by the law;

፯/ "በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ያፈራው ንብረት" ማለት በራሱ ስም የሚገኝ ንብረት፣ በራሱ ስም ባይሆንም ለራሱ ጥቅም ሲያዝበት ወይም ሲቆጣጠረው የነበረው ንብረት፣ የተጠቀመው ወይም ያስወገደው ንብረት፣ በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ያስተላለፈውን ንብረት ይጨምራል፤

7/ "direct or indirect generated asset" means an asset found in his name or an asset to which he effectively controlled for the benefit of himself or an asset he consumed or disposed or an asset transferred through sale, donation or on any other means;

፰/ "በጥፋተኝነት ላይ የተመሰረተ መውረስ" ማለት ተከሳሹ በፍርድ ቤት በወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎ በተወሰነ ጊዜ ውሳኔውን መሠረት በማድረግ የሚከናወን የንብረት መውረስ ነው፤

8/ **"Conviction Based Confiscation"** means confiscation of an asset following the conviction of an accused and decision by a court of law;

፱/ "በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ መውረስ" ማለት በማንኛውም ዓይነት ወንጀል በፍርድ ቤት ውሳኔ ጥፋተኛ ባይባልም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከናወን የንብረት መውረስ ነው፤

9/ **"Non-Conviction Based Confiscation"** means confiscation of an asset pursuant to this proclamation despite the accused is not convicted of any crime;

፲/ "ማገድ" ማለት በፍርድ ቤት ወይም ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠው ውሳኔ ፀንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ንብረቱ እንዳይተላለፍ፣ ወደሌላ እንዳይለወጥ፣ እንዳይወገድ መከልከል ነው፤

10/ **"Freezing"** means prohibiting the transfer, conversion, disposition, or movement of the asset on the basis of, and for the duration of the validity of the decision of the court or other Authorized body;

፲፩/ "መያዝ" ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠው ውሳኔ ፀንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ንብረቱ እንዳይተላለፍ፣ ወደሌላ እንዳይለወጥ፣ እንዳይወገድ ወይም እንዳይንቀሳቀስ መከልከል እና ከንብረቱ ጋር ተዛማጅነት ባለው ተቋም ወይም በንብረት አስተዳዳሪ ቁጥጥር ወይም ይዞታ ስር እንዲተዳደር ማድረግ ነው፤

11/ **"Seizure"** means prohibiting the transfer, conversion, disposition, or movement of the asset on the basis of, and for the duration of the validity of the decision of the court or other Authorized body while the administration of such asset is under the control or possession of **an inistitution relates with the asset** or the asset manager;

፲፪/ "ምናባዊ ንብረት" ማለት በዲጂታል መንገድ ለመገበያየት፣ ለማስተላለፍ ወይም ለኢንቨስትመንት ክፍያ ሊያገለግል የሚችል ሲሆን በዲጂታል የሚወከሉ የመገበያያ ገንዘብን፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋየ እና ሌሎች ተላላፊ የሆኑ የክፍያ ሰነዶችን አይጨምርም፤

12/ **"Virtual Asset"** means a digital representation of value that can be digitally traded or transferred, and can be used for payment or investment purposes. However, this does not include digital representation of fiat currencies, securities and other negotiable instruments;

፲፫/ "ጠቋሚ" ማለት በወንጀል ድርጊት ከተገኘ ንብረት ወይም ምንጩ ካልታወቀ ንብረት ጋር በተያያዘ በምርመራ ወይም በክስ ሂደት መረጃ የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ ሰው ነው፤

13/ **"Whistleblower"** means a person who agrees to give or gives information related to assets obtained from a crime or unexplained asset at the time of investigation or during the trial;

፲፬/ "መርማሪ" ማለት በሚኒስቴሩ ስር በመርማሪነት የተቀጠረ እና የንብረት ማስመለስ ምርመራ ስራን የሚሰራ ባለሙያ ነው፤

14/ **"Investigator"** means an investigation expert hired by the Ministry and who conducts asset investigation;

፲፭/ "ዐቃቤ ሕግ" ማለት በሚኒስቴሩ ውስጥ በዐቃቤ ሕግነት ሙያ የተቀጠረ እና የንብረት ማስመለስ ምርመራ እና የክስ ስራን የሚሰራ ባለሙያ ነው፤

15/ **"Prosecutor"** means a professional employed as a prosecutor in the Ministry and engaged in asset recovery investigations and prosecutions;

፲፮/ "የንብረት ምርመራ" ማለት ንብረት ለማስመለስ የሚደረግ ምርመራ ነው፤

16/ **"Investigation"** means an investigation that is carried out to recover an asset;

፲፯/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የፍትህ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

17/ **"Ministry or Minister"** means Ministry of Justice or the Justice Minister respectively;

፲፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤

18/ **"Person"** means any natural or legal person;

፲፱/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

19/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ፡-

3. <u>Scope of Application</u>

This proclamation:

፩/ "በወንጀል ሕጉ ወይም በሌሎች ሕጎች መሠረት ወንጀሉን መክሰስ የኢትዮጵያ ሥልጣን በሆነ ጊዜ ንብረትን ለማስመለስ፤ ወይም

፪/ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ማስመለስ ሂደት ላይ፤

ተፈፃሚ ይሆናል።

፬. የሕግ ሰውነት ያላቸው ተቋማትን በተመለከተ

፩/ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ አንቀፅ ፴፬ ቢኖርም የመንግስት ተቋማትን ሳይጨምር የሕግ ሰውነት ያለው ማንኛውም ድርጅት በማንኛውም ሁኔታ በወንጀል ድርጊት አማካኝነት ንብረት ማግኘቱ ወይም ለሌላ ሰው ማስገኘቱ ወይም በሌላው ሰው ጥቅም ላይ ጉዳት ስለማድረሱ ጠቋሚ ማስረጃ ከተገኘ የንብረት ማስመለስ ሂደቱ በዚህ ሕግ መሠረት ይመራል።

፪/ "የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም አዋጁ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን በተመለከተ በመንግስት ተቋማት፣ በሃይማኖት ድርጅት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች እና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

ክፍል ሁለት

ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ስለማስመለስ

፭. ምንጩ ያልታወቀ ንብረት

የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፯ ድንጋጌዎች ላይ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ኃላፊነት ያለባቸው አካላት እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው፡-

፩/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያለው ንብረት ወይም የኑሮ ደረጃው አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት ስራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ የማይመጣጠን እንደሆነ እና የንብረቱን ወይም የኑሮ ደረጃውን ምንጭ በተመለከተ ምክንያታዊ የሆነ የወንጀል ጥርጣሬ በኖረ ጊዜ የዚህ ዓይነቱ የኑሮ ደረጃ ወይም ያለው ንብረት እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር ንብረቱ ይወረሳል፤

1. shall be applicable to asset recovery where Ethiopia has jurisdiction to prosecute the crime under the criminal law or other applicable laws.

2. shall be applicable to asset recovery cases on unexplained asset.

4. Asset Recovery on Legal Persons

1. Notwithstanding the provision of Article 34 of the Criminal Code, legal persons other than government institutions are subjected to asset recovery laws pursuant to this Proclamation if there is evidence indicating that they obtain or procure for another undue advantage of an asset from any criminal activity or cause damage to the interest of other persons.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, this proclamation may not be applicable to government inistitutions, religious, political and international organizations regarding unexplained asset.

PART TWO

RECOVERY OF UNEXPLAINED ASSET

5. Unexplained Asset

Without prejudice to the accountability of persons responsible for unexplained asset under the Anti-Corruption Proclamations No 881/2007, any person:

1/ who is directly or indirectly in control of an asset or maintains a lifestyle disproportionate to the legitimate income from his present or past occupation or other legal means and when there is a reasonable suspicious for a crime, unless he proves to the satisfaction of the court how he was able to maintain such standard of living or how such asset came under his control, the asset shall be confiscated;

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሕጋዊ ገቢ እንዳለው የሚያስረዳ የተመዘገበበት ሥርዓት የሌለው ወይም ገቢው አነስተኛ በመሆኑ ከግብር ነፃ የሆነ ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያለው ንብረት ወይም የኑሮ ደረጃው ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ የማይመጣጠን እንደሆነ የዚህ ዓይነቱ የኑሮ ደረጃ ወይም ያለው ንብረት እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር ንብረቱ ይወረሳል::

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, whosoever has no legally registered means of proving income or persons excempted from tax payment because of their low income but directly or indirectly controls an asset or maintains a lifestyle disproportionate to the legitimate income from his present or past occupation shall be confiscated, unless he proves to the court about how such asset or life style is obtained.

፮. ምንጩ ያልታወቀ ንብረት የቅድመ ክስ ሥርዓት

6. Pretrial Hearing of the Unexplained Asset

፩/ ዐቃቤ ሕግ ምንጩ ያልታወቀ ነው ብሎ የጠረጠረውን ማንኛውንም ንብረት ዝርዝር እና የተገኘበትን አግባብ የሚያሳይ መግለጫ እንዲያቀርብ በጽሁፍ ጥያቄ የቀረበለት ማንኛውም ሰው ጥያቄው በደረሰው በ፪ ወራት ጊዜ ውስጥ ለዐቃቤ ሕግ ዝርዝር ማስረጃዎችን በማያያዝ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል::

1/ Where the prosecutor requests any person to disclose details of assets and the means of acquisition thereto in writing for suspecion of unexplained asset, the requested person shall give a written response with evidence within two month from the receipt of the request.

፪/ የንብረቱን ምንጭ እንዲያስረዳ የተጠየቀው ሰው የንብረቱን ምንጭ ለማስረዳት የሚያቀርበው ማስረጃ ሕጋዊ መሆን አለበት::

2/ The requested person shall only submit legal evidences to prove the legitimate source of the asset.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ማስረጃዎችን ለማቅረብ የተመለከተው የአንድ ወር የጊዜ ገደብ አስገዳጅ ሁኔታ ሲኖር ለዐቃቤ ሕግ በሚቀርብ አቤቱታ ሊራዘም ይችላል፤ ሆኖም ይህ የጊዜ ገደብ ከስድስት ወር ሊበልጥ አይችልም::

3/ The one month time limit to provided evidences under Sub- Article (1) of this Article may be extended due to compelling situations requested by the party but it may not exceed six months.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ዝርዝር ማስረጃ እንዲያቀርብ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረበ ንብረቱ ምንጩ ያልታወቀ ነው የሚል ግምት ተወስዶበት ዐቃቤ ሕግ ንብረቱ እንዲወረስ ክሱን ለፍርድ ቤት ያቀርባል::

4/ When the requested party fails to disclose the evidence requested as per Sub-Article (1) of this Article, the prosecutor will apply the case to the court presuming that the property is unexplianed wealth.

፭/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረቡ ዝርዝር ማስረጃዎች ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን የተመለከተ ክስ ሲቀርብ በፍርድ ቤት ማስረጃ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል::

5/ Any evidence obtained pursuant to Sub-Article (1) of this Article can be used as evidence in unexplained asset proeeding.

፯. በራስ ላይ ማስረጃ ስለማቅረብ

7. Self-incrimination

፩/ የንብረቱን ምንጭ እንዲያስረዳ የተጠየቀው ሰው የንብረቱን ምንጭ ለማስረዳት የወንጀል ኃላፊነት የሚያመጣበት ማስረጃ ቢሰጥም በወንጀል ችሎት በራሱ ላይ ማስረጃ ሆኖ አይቀርብም::

1/ Self-incriminating evidence obtained to the compliance of such unexplained asset disclosure shall not be presented against the person before a court of law in criminal proceedings.

፪/ የንብረቱን ምንጭ እንዲያስረዳ የተጠየቀው ሰው ሀሰተኛ ማስረጃ ካቀረበ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተሰጠውን መብት መጠቀም አይችልም።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ የተፈጸመውን ወንጀል በሌሎች ማስረጃዎች ከማስረዳት አይከለከልም።

2/ If a person, who is requested to explian the source of the asset, presents a forged document cannot use any right in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the prosecutor shall not be prohibited to prove the crime by evidence obtained through other means.

፰. ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ክስ የሚቀርብበት ጊዜ እና የገንዘብ መጠን

8. The Time and Threshold for Unexpalined Asset Claim

፩/ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ከመሆኑ በፊት ባሉት አስር ዓመት ውስጥ ወይም ተፈፃሚ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የተገኘ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን ለማስመለስ በዚህ አዋጅ መሠረት ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ክስ ሊቀርብ ይችላል።

1/ Asset recovery claim on unexpained asset may be brought to the Court on assets obtained back 10 years from the promulgation of this Proclamation or from the effective date of this Proclamation.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አዋጁ ተፈፃሚ ከመሆኑ በፊት ባለው አስር ዓመት ውስጥ በተገኘ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ላይ ክስ የሚቀርበው ምንጩ ያልታወቀው የንብረቱ ግምት ከብር አስር ሚሊዮን በላይ ከሆነ ነው።

2/ Unexplained asset recovery claim 10 years back to this Proclamation persuant to Sub-Article (1) of this Article, shall be brought to the court, when the amount of unexplained asset is more than 10 million birr.

ክፍል ሶስት

ስለንብረት ምርመራ

PART THREE

ASSET INVESTIGATION

፱. የንብረት ምርመራ አጀማመር

9. Starting Investigation

ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ በተሟላ ጊዜ በዓቃቤ ሕግ ወይም በመርማሪ የንብረት ማስመለስ ምርመራ ይጀመራል፡-

The public prosecutor or the investigator may initiate an asset recovery investigation when any of the following conditions are met:

፩/ በሕግ የወንጀል ምርመራ ሥልጣን ከተሰጣቸው ተቋማት ወይም ከሌሎች የመንግስትና የግል ተቋማት በሚመጣ ጥቆማ ወይም መረጃ፤

1/ information or evidence comes from crime investigation authorities mandated by law or from government or private institutions;

፪/ መረጃ ያለው ማንኛውም ሰው በሚሰጠው ምክንያታዊና አሳማኝ ጥቆማ፤

2/ reasonable and reliable information comes from any whistleblowers;

፫/ ከፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ወይም ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት በሚቀርብ ጥቆማ ወይም መረጃ ፤ ወይም

3/ information or evidence comes from financial intelligence services or other financial institutions;

፬/ በማንኛውም ሁኔታ የንብረት ማስመለስ ምርመራ ሊጀመር የሚችልበት በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን።

4/ there is a sufficient reason to begin an asset recovery investigation on its own initiative or in any circumstances.

፲. ጠቅላላ የንብረት ምርመራ ዘዴ

በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና በሌሎች ልዩ ሕጎች የምርመራ ዘዴን በተመለከተ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ የንብረት ምርመራ በሚያከናውንበት ጊዜ የሚከተሉትን የምርመራ ዘዴዎች ሊጠቀም ይችላል፡-

፩/ የገንዘብ ፍሰት ሰነዶችና ምናባዊ ንብረት ምርመራ፣

፪/ የቀረጥና የግብር ሰነዶች ምርመራ፣

፫/ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሰነዶች ምርመራ፣

፬/ የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት ወይም ሪል እስቴትን የሚመለከት ማንኛውም ምርመራ፣

፭/ የጉዞ ሰነዶች፣ የፓስፖርት ወይም የወሳኝ ኩነቶች ሰነድ ምርመራ፣

፮/ የሀብት ምዝገባ ሰነዶች ምርመራ፣

፯/ የካፒታል ገበያ መረጃዎች ምርመራ፣ ወይም

፰/ ሌሎች ለንብረት ማስመለስ ሊያገለግሉ የሚችሉ ማናቸውንም የምርመራ ዘዴዎች።

10. General Investigation Techniques

Without prejudice to the investigation techniques recognized by the Criminal Procedure Code and other laws, the public prosecutor or the investigator may apply the following techniques for asset investigation:

1/ financial transaction documents and vertual asset investigation;

2/ customs and tax documents investigation;

3/ trade registration and license investigation;

4/ immovable, movable or real estate investigation;

5/ travel documents, passport, vital events registration documents investigation;

6/ asset registration documents investigation;

7/ capital market documents investigation;

8/ other techniques that may be relevant for asset recovery investigation.

፲፩. ልዩ የንብረት ምርመራ ዘዴ

፩/ የወንጀል ፍሬ ወይም ከወንጀል ድርጊት ጋር የተገናኘ ማንኛውም ንብረት መኖሩን የሚመለከት ማስረጃ ለማግኘት ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ አግባብነት ካለው ተቋም ጋር በመተባበር የሚከተሉትን ልዩ የምርመራ ዘዴዎች በመጠቀም ማስረጃ ለመሰብሰብ ይችላል፡-

ሀ) በባንክ ሂሳቦችና በሌሎች ተመሳሳይ ሂሳቦች ላይ ክትትል በማድረግ፣

ለ) የኮምፒውተር ሥርዓቶችን፣ መረቦችንና ሰርቨሮችን በማየት ወይም በመድረስ፣

ሐ) በፖስታ፣ በደብዳቤ፣ በቴሌፎን፣ በፋክስ፣ በራድዮ፣ በኢንተርኔት ወይም በሌሎች ማናቸውም የመገናኛ ዘዴዎች ወይም መሣሪያዎች የሚደረጉ ልውውጦችን ወይም ግንኙነቶችን በክትትል ስር በማዋል ወይም በመጥለፍ፣

11. Special Investigation Techniques

1/ For the purpose of obtaining evidence regarding the existance of any property related to crime or proceeds of crime, a prosecutor or investigator may collect evidence incollaboration with relevant institutions using the following special investigation methods:

a) To monitor bank accounts and other similar accounts;

b) to access computer systems, networks and servers;

c) to place under surveillance or to intercept postal communication, letters, telephone, fax, radio, internet or any other communication systems;

መ) ድርጊቶችን፣ የኑሮ ዘይቤውን፣ ንግግሮችን በድምጽ ወይም በምስል በመቅረጽና ፎቶግራፍ በማንሳት፤

ሠ) በሽፋን ውስጥ የሚደረግ ምርመራ በማድረግ፤

ረ) በቁጥጥር ውስጥ የሚደረግ ምርመራ በማድረግ።

d) to take audio or video recordings of acts, behaviors, conversations or lifestyle or take photograph;

f) to conduct undercover operation; and

g) to conduct controlled delivery.

፪/ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ስር የተደነገጉ ልዩ የማስረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ የሚችለው ፍርድ ቤት የምርመራውን አስፈላጊነት ሲፈቅድ ብቻ ነው።

2/ The investigation techniques stipulated under Sub-Article (1) of this Article may only be used by the investigator or prosecutor when the court belives and approves the nessesity of the techiniques.

፫/ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ለቀረበ ጥያቄ የሚፈቅደው ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪው በመደበኛው የምርመራ ዘዴ ሊገኙ የማይችሉ ማስረጃዎች መሆናቸውን የሚጠቁም ምክንያት መኖሩን ለፍርድ ቤቱ ሲያስረዳ ነው።

3/ The techniques mentioned in Sub-Article (2) of this Article shall only be authorized if the public prosecutor or investigator can demonstrate reasonable grounds that such evidence cannot be obtained through alternative investigative methods.

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመው ለሚኒስትሩ ወይም ሚኒስትሩ ለወከለው ኃላፊ በማስፈቀድ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በልዩ የንብረት ምርመራ ዘዴ ማስረጃ ሊሰበስብ ይችላል።

4/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, in urgent situtions, the prosecutor or investigator may collect evidence through special incvestigation techiniques without Court authroization upon persmission by the Minister or the head represented by the Minister.

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) መሠረት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በልዩ የንብረት ምርመራ ዘዴ ማስረጃ ለመሰብሰብ በተጀመረ በ፵፰ ሰዓት ውስጥ ምክንያቶቹንና የተሰጠውን ጊዜያዊ ፈቃድ ጨምሮ ለፍርድ ቤት በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፤ ፍርድ ቤቱም የጥያቄውን አግባብነት መርምሮ ለመቀበል ወይም ውድቅ ለማድረግ ይችላል።

5/ Persuant to Sub-Artivle (4) of this Article, the prosecutor or investigator shall submit the reason and the permission in writing to the Court with in 48 hours starting the collection of evidence. The Court examines the relevancy of the request and may accept or reject it.

፲፪. <u>ማስረጃ እንዲቀርብ ወይም እንዲገለፅ የመጠየቅ ሥልጣን</u>

12. <u>Power to Require Production or Disclosure of Evidence</u>

፩/ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ከወንጀል የተገኘ ንብረት ወይም ለወንጀል ድርጊት መፈፀሚያነት የዋለ ንብረት ስለመኖሩ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው በማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ይዞታ ወይም ባለቤትነት ስር የሚገኝ ንብረትን በተመለከተ ማንኛውም ማስረጃ እንዲቀርብለት ወይም እንዲገለፅለት በጽሁፍ ሊጠይቅ ይችላል።

1/ When the public prosecutor or investigator has reasonable doubt about the existence of proceeds of crime or instrumentalities of crime, it may ask any person in writing to provide or disclose such evidence regarding property that is in the possession or ownership of any person.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የሚጠየቀው ማስረጃ ወይም እንዲገለፅ የተፈለገው ጉዳይ የሚገኘው በማንኛውም የመንግስት ወይም መንግስታዊ ባልሆነ ተቋም ውስጥ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪው ይህንኑ ማስረጃ መጠየቅ ይችላል።

2/ If the evidence required as per Sub-Article (1) of this Article is found in any government institution, the public prosecutor or investigator may request such evidence.

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ወይም (፪) መሠረት ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም ስለተጠየቀው ነገር እንዲገልፅ የሚጠየቅ ማንኛውም ሰው፤ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ማስረጃው በሚገኝበት ሁኔታ የማቅረብ ወይም የመግለፅ ግዴታ አለበት።

3/ Persuant to Sub-Article (1) or (2) of this Article, any person, governmental or non governmental institutions requested to provide or dislose evidence about the reguested matter shall be obliged to provide or dislose the evidence as it is availabel.

፬/ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ማስረጃ እንዲቀርብለት ወይም እንዲገለፅለት የሚያቀርበው ጥያቄ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦

4/ The written request made by the Public Prosecutor or Investigator for the production or disclosure of evidence may include to:

ሀ) ማስረጃ የተጠየቀው አካል በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ እንዲያቀርብ፤

a) produce or disclose evidence at such time and place specified;

ለ) ለቀረቡለት ጥያቄዎች መልሱን በተወሰነ ጊዜና ቦታ እንዲመልስ፤

b) answer questions at such time and place specified;

ሐ) ማንኛውም የሚፈለግ ማስረጃ በይዞታው የሚገኝ አካል በይዞታው የሚገኙ ሰነዶችን፣ መዛግብቶችን፣ የኤሌክትሮኒክ መረጃዎችን በመርማሪው አካል እንዲታዩ እንዲመረመሩ ወይም ከዋናው ማስረጃ ጋር የተገናዘበ ቅጅ እንዲያቀርብ።

c) any one who have important evidence permit the investigator to have access to and investigate or provide verified copies of any documents, archives, and electronic data containing the required information.

፲፫. መረጃ አሳልፎ መስጠትን ስለመከልከል

13. Prohibition of Tipping-off

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው አግባብ ስራውን ሲያከናውን ያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ወይም ማስረጃ፦

1/ Any person who gets information or evidence while performing his duties under this Proclamation may not disclose or transfer it to any party unless:

ሀ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው ሁኔታ ስራውን በተገቢው መንገድ ለማከናወን እንዲረዳው ካልሆነ፤

a) for the purpose of conducting the duties in proper way according to this Proclamation;

ለ) በፍርድ ቤት ካልታዘዘ፤ ወይም

b) ordered by the Court; and

ሐ.) ከሚኒስትሩ የጽሁፍ ፍቃድ ካላገኘ፤

c) granted written permission from the Minister.

በስተቀር ለማንኛውም ሰው መግለፅ ወይም አሳልፎ መስጠት አይችልም።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ስር የተደነገገውን ክልከላ የተላለፈ ሰው አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፡፡

2/ Any person who is found in violation of Sub-Article (1) of this Article shall be liable according to relevant criminal law provisions.

፲፬. የማስረጃ ምዘና ሥነ-ሥርዓት

14. Standard of Proof

፩/ በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ዓይነት የንብረት ማስመለስ ወይም ውርስ ጉዳይ የሚታየው በፍትሃ-ብሄር ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ሲሆን የማስረዳት ምዘናው በፍትሃብሄር ክርክር ጊዜ እንደሚቀርበው የማስረጃ ደረጃ ይሆናል፡፡

1/ Unless otherwise provided in this Proclamation, any kind of asset recovery or confiscation shall follow Civil Procedure and the standard of proof shall be Civil Standard.

፪/ በወንጀል ምርመራ ወይም በወንጀል ፍርድ ሂደት የተገኘ ማስረጃ ለንብረት መውረስ ዓላማ በማስረጃነት ይቀርባል፡፡

2/ Any evidence obtained in the crime investigation or criminal proceeding shall be used as evidence for asset recovery proceedings.

፫/ በወንጀል ክርክር ሂደት አልፎ የመጨረሻ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በዚህ ሂደት የቀረበ ማስረጃ በድጋሚ የማስረጃ ምዘና ሂደት ማለፍ ሳያስፈልገው የንብረት ማስመለስ ክርክሩን ለሚመለከተው ችሎት ሊስተባበል የማይችል ማስረጃ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

3/ When a final conviction is given in a criminal proceeding, the evidence adduced in the process, shall be considered as final evidence without re-evaluating for the purpose of asset recovery proceedings.

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ክርክሩ ያልተካተቱ ተጨማሪ ማስረጃዎች ለንብረት ማስመለስ ክርክር ከማቅረብ የሚከለከል አይሆንም ፡፡

4/ Without prejudice to Sub-Article (3) of this Article, adducing additional evidence on asset recovery proceeding, which was not part of the criminal proceeding is not prohibited.

ክፍል አራት

ስለንብረት ማገድ ወይም መያዝ

PART FOUR

ASSET FREEZING AND SEIZURE

፲፭. ስለማገድ ወይም መያዝ

15. Freezing or Seizure

፩/ የንብረት መውረስ ሊያስከትል የሚችል ምርመራ እየተካሄደ ከሆነ፣ ክስ ከቀረበ፣ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ ወይም ሌላ በቂ የሆነ ምክንያት ሲኖር ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ንብረቱ እንዲታገድ ወይም እንዲያዝ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

1/ Where there is an investigation that may lead to asset confiscation, a charge is filed, conviction is obtained, or where there is any other sufficient reason, application for freezing or seizure may be made to the Court by the public prosecutor or the investigator.

፪/ ሚኒስትሩ ወይም በሚኒስትሩ የሚወከል ኃላፊ የሚታገደው ንብረት በተፋጠነ ሁኔታ ሊሸሽ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ሊያሳጣው የሚችል ድርጊት መኖሩን ሲያምንበት ንብረቱን ለሶስት የሥራ ቀናት እንዲታገድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ The Minister or the head delegated by the Minister may give a freezing order on the asset for three working days when it's believed that the assets might be squandered or the economic value of the asset may vanish.

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ባሉት ሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ የፍርድ ቤት እግድ ካልተጠየቀ ትዕዛዙ በራሱ ጊዜ ቀሪ ይሆናል።

3/ Unless otherwise a Court order is requested within the three working days, the freezing order given under Sub-Article (2) of this Article shall be ceased.

፬/ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በተጠቀሰው ሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ የፍርድ ቤት እግድ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ አቤቱታ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ የእግዱ ትዕዛዝ ፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ እንደፀና ይቀጥላል።

4/ Where the public prosecutor or investigator has submitted an application to the Court within the three working days, the freezing order shall stand until a decision is to be given by the Court.

፭/ ዓቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) መሠረት ለፍርድ ቤት የቀረበውን የእግድ አቤቱታ ትዕዛዝ ለተቀበለው ተቋም ያሳውቃል።

5/ Persuant to Sub-Article (4) of this Article, the public prosecutor or investigator shall inform the instituion that has recived the freezing order about the submission of the application to the Court.

፮/ የማገድ ትዕዛዝ ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ መወሰን አለበት።

6/ The Court that receives an application for the freezing order shall give a decesion within fifteen days from the date of application.

፲፮. <u>ንብረት እንዲታገድ ወይም እንዲያዝ የሚጠየቅበት ሁኔታ</u>

16. <u>Condition to Request for Freezing or Seizure</u>

፩/ ንብረት ለማስመለስ በሚደረግ ሂደት በሚከተሉት ምክንያቶች ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ንብረቱ ታግዶ እንዲቆይ ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፦

1/ In the process of asset recovery, the prosecutor or the investigator may request the Court for freezing order in any of the following conditions:

ሀ) ንብረቱ በማንኛውም ሰው ይዞታ ውስጥ ቢቆይ በንብረቱ ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳት የማይኖር ከሆነ፤

a) when it would not be damaged under anyone's possession; or

ለ) ለንብረቱ ኢኮኖሚያዊ ጥበቃ የተሻለ እንደሆነ፤ ወይም

b) where it is important to the economic value of the asset; or

ሐ) በንብረቱ ልዩ ባህሪ ምክንያት ባለበት መቆየቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ።

c) where it is necessary to keep on the site due to the nature of the asset.

፪/ ንብረት ለመውረስ ወይም ለማስመለስ በሚደረግ ሂደት ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ንብረቱ እንዲያዝ ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል፦

2/ In the process for confiscation, a seizure order may be given under any of the following conditions when:

ሀ) ተጠርጣሪው በታገደው ወይም በሚያዘው ንብረት ላይ ጉዳት ያደርሳል፣ ንብረቱን ይሰውራል ወይም ተጨማሪ ወንጀል ሊፈፅምበት ይችላል ተብሎ ሲታመን፤

a) there are suspicious grounds to believe that the suspect may damage the asset, hide it or commit further crime using the asset;

ለ) ንብረቱ የወንጀል ፍሬ ስለመሆኑ ወይም ለወንጀል መፈፀሚያነት የዋለ ስለመሆኑ ለመጠርጠር የሚያስችል አሳማኝ ጠቋሚ ማስረጃ ሲኖር፤

ሐ) ከወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ንብረት ባልተገኘ ጊዜ ወይም ቀድሞ የሸሸ እንደሆነ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚወረሰው ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ሕጋዊ ንብረት ሲገኝ፤

መ) በሚሰጥ የእግድ ትዕዛዝ መሠረት ንብረቱ ላይ ሊደርስ የሚችል ማንኛውንም ዓይነት ጉዳት መከላከል የማይቻል በሆነ ጊዜ።

፫/ የንብረት የማገድ ወይም የመያዝ አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ በተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ስም ከሚገኝ ንብረት በተጨማሪ በትዳር ጓደኛ፣ ሳይጋቡ እንደባልና ሚስት በሚኖሩ ሰዎች መካከል ወይም በልጆች ስም የሚገኝ ተመጣጣኝ ንብረት እንዲታገድ ወይም እንዲያዝ ማመልከቻ ሊቀርብ ይችላል።

፬/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በማንኛውም ግለሰብ የሚገኝ ንብረት በወንጀሉ ከተገኘው ንብረት ጋር ወይም ለወንጀል መፈፀሚያ ከዋለው ንብረት ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን ከጠረጠረ የግለሰቡ ንብረት እንዲታገድ ወይም እንዲያዝ ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል።

፲፯. <u>ንብረት እንዲያዝ ወይም እንዲታገድ የሚቀርብ ማመልከቻ አቀራረብና ይዘት</u>

ንብረት የመያዝ ወይም የእግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

፩/ የንብረት ምርመራው ፍሬ ነገርና በየደረጃው የተወሰዱትን እርምጃዎች፣ ክስ ያልተመሰረተ ከሆነ ጉዳዩ የሚገኝበትን ደረጃ የሚያሳይ መረጃ፤

፪/ የሚያዘው ወይም የሚታገደው ንብረት ተፈፅሟል በተባለውና ምርመራ በተጀመረበት ወንጀል አማካኝነት ተጠርጣሪው ያገኘው የወንጀል ፍሬ፣ የወንጀል መፈፀሚያ ንብረት፣ ወይም የደረሰ ጉዳትን በሚመለከት አሳማኝ ምክንያት፤

b) there is prima facie evidence that indicates the asset is the proceeds or instrumentalities of the crime;

c) the proceeds of the crime cannot be found or transferred, as it is necessary, the proportional value of the suspect's legal asset;

d) it is impossible to prevent any kind of damage on the asset through freezing.

3/ In addition to the property in the name of the accused or the suspect, an pplication may be submitted for the freezing of proportinal value of the asset in the name of the spouse, the partner under irregular union or children.

4/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (3) of this Article, an application may be made to the Court for the freezing or seizure of any person's asset suspected to have connection with the proceeds or instrumentalities of the crime.

17. <u>Form of Application and Content for Freezing or Seizure of Asset</u>

Application for the freezing or seizure orders shall be accompanied by an affidavit and shall include:

1/ The asset investigation material facts and measures taken in each phase; the status of the case if a charge is not opened;

2/ Sufficient reasons that demonstrate the asset is obtained from crime or proceeds of crime, instrumentality of crime or damaged caused due to the alleged crime that has initiated an investigation;

፫/ የሚያዘው ወይም የሚታገደው ንብረት የሚታወቅ በሆነ ጊዜ የንብረቶችን ዝርዝር አድራሻ፤

የያዘ መሆን አለበት፡፡

3/ Details of the address of the assets to be seized or frozen when it is known.

፲፰. <u>ንብረት እንዲያዝ ወይም እንዲታገድ በቀረበ ማመልከቻ ላይ ስለሚሰጥ ትዕዛዝ</u>

፩/ ንብረት እንዲያዝ ወይም እንዲታገድ ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት የቀረበውን ማመልከቻ መርምሮ፡-

ሀ) ንብረቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲታገድ፤

ለ) ንብረቱ በሙሉ ወይም በከፊል በሚኒስቴሩ ስር እንዲሆን ወይም እንዲያዝ፤

ሐ) አስተዳዳሪ እንዲሾም፤ ወይም

መ) ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ውሳኔዎች፤ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ መሠረት የሚሰጠውን ትዕዛዝ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በንብረቱ ላይ ሕጋዊ የባለቤትነት መብት ላለው ሰው ያሳውቃል፡፡

18. <u>Conditions for Freezing or Seizure Orders</u>

1/ The Court to which an application has been made to seize or freeze the asset shall examine the application submitted and give order:

a) for the freezing of the asset either partially or in full;

b) for the seizure of the asset or to be placed under the control of the Ministry either partially or in full;

c) for the appointment of the asset manager; or

d) other appropriate measures.

2/ The public prosecutor or investigator shall notify the Court order given pursuant to Sub-Article (1) of this Article to the legally recognized owner of the asset.

፲፱. <u>የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ስለመመዝገብ</u>

በንብረቱ ላይ ያለ መብት እንዲመዘገብ የሚያስገድድ ሕግ ያለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ ንብረቱን የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ተቋም ትዕዛዙ እንደደረሰው ዝርዝር ይዘቱን ወዲያውኑ መመዝገብ አለበት፡፡

19. <u>Registration of Court Orders</u>

Where there is a legal requirement for asset registration, the freezing or seizure order issued by the Court must be expeditiously registered by the appropriate authority upon receiving the order.

፳. <u>የእግድ ወይም የመያዣ ትዕዛዝ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፰ በተደነገገው መሠረት በንብረቱ ላይ የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ የተሰጠ እንደሆነ ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በተጠርጣሪው ላይ ከንብረቱ ጋር በተያያዘ የተጠረጠረበት የወንጀል ክስ ወይም ንብረቱን የማስወረስ ክስ ካልቀረበ ሌላ ምክንያት መጥቀስ ሳያስፈልግ ጊዜውን መሠረት በማድረግ ብቻ የተሰጠው የመያዝ ወይም

20. <u>Validity Period of Freezing or Seizure Orders</u>

1/ The asset owner or suspect may apply to the Court for revocation of a freezing or seizure order issued in accordance with Article 18 of this Proclamation, without requiring further justification, unless a criminal charge pertaining to the asset or a confiscation process is filed against the susprct within one year from the date of the order.

የእግድ ትዕዛዝ ቀሪ እንዲሆን ባለንብረቱ ወይም ተጠርጣሪው ለፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ንብረቱ የታገደበት ወይም የተያዘበት ወይም በንብረቱ ላይ ጥቅም ወይም መብት አለኝ የሚል ማንኛውም ሰው የጊዜ ገደቡን መሠረት ሳያደርግ በሌሎች ምክንያቶች የሚያቀርበውን የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ ይነሳልኝ አቤቱታን የሚያስቀር አይደለም።

፫/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የቀረበው ማመልከቻ ላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግ እና አስተያየቱን በማገናዘብ የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዙ እንዲነሳ ሊወስን ይችላል።

፬/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም የንብረቱ ተይዞ ወይም ታግዶ መቆየት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መሆኑን ባመነበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ለሚለው ተጨማሪ ጊዜ ንብረቱ ታግዶ ወይም ተይዞ እንዲቆይ ሊወስን ይችላል።

2/ The provision of Sub-Article (1) of this Article may not preclude any person who claims to have an interest or right in the frozen or seized asset, from submitting a petition to revoke the order based on reasons other than the time limit.

3/ The Court may withdraw the freezing or seizure order persuant to Sub-Article (1) of this Article after considering the opinion of the prosecutor or the investigsstor.

4/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (3) of this Article, even if the withdrawal of the freezing or seizure order may be given, in the interest of justice, the Court may sustain the order for an additional period deemed appropriate by the Court.

፳፩. ስለ ማገድ እና መያዝ ይግባኝ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ፍርድ ቤቱ በንብረቱ ላይ የሰጠውን የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል በወሰነ ጊዜ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ውሳኔውን በመቃወም ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለው።

፪/ ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ይግባኝ የጠየቀ እንደሆነ፥ ንብረቱ እንዳይለቀቅ ይግባኝ ስለመጠየቁ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ይግባኝ የጠየቀበትን አቤቱታ ወይም ማመልከቻ ማቅረብ አለበት። ፍርድ ቤቱም ማስረጃው እንደደረሰው ይግባኙ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ቀድሞ የሰጠው የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ ፀንቶ እንዲቆይ ትዕዛዝ ይሰጣል።

21. Appeal on Freezing or Seizure

1/ When the Court decides for the withdrawal or amendement of the order pursuant to Sub-Article (2) of Aricle 20 of this proclamation, the prosecutor or invistegator has the right to appeal on the decesion of the Court.

2/ The freezing or seisure order shall remain in force until a final decesion is given by the Appellate Court if an apeal is made persuant to Sub-Article (1) of this Article and where the prosecutor or the insvestigator produce the petition of such appeal to the the Court that issued the decision within five working days from the date of filing the appeal.

፫/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ይግባኝ ስለመጠየቁ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ማስረጃ ካልቀረበለት የተያዘው ወይም የታገደው ንብረት እንዲለቀቅ ይወስናል።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሠረት የተቀመጠው የአምስት ቀን የጊዜ ገደብ የሚቆጠረው ዐቃቤ ሕግ የውሳኔው ግልባጭ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ነው።

3/ The Court may release the asset frozen or seized if the prosecutor or investigator does not submit the evidence about the request for appeal pursuant to Sub-Article (2) of this Article.

4/ The five days time limit shall be counted after the day when the public prosecutor recieves the copy of the Court decision.

፳፪. ያለእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ የማይሰጥበት ንብረት

22. Exempted Assets from Freezing or Seizure

፩/ በዚህ አዋጅ ስለንብረት ማገድና መያዝ የተደነገገው ድንጋጌ ቢኖርም፡-

1/ Without prejudice to provisions about freezing and seizure in this proclamation, the Court may not give freezing or seizure orders on the following assets:

ሀ) የተጠርጣሪው፣ የተከሳሹ፣ የፍርደኛው ወይም በስሩ ለሚተዳደሩ የቤተሰብ አባላት የእለት መተዳደሪያ ወይም ሙያዊ ስራ ለመስራት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች እና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች፤

a) The tools essential for the suspect's, accused's, or their dependent family members' daily livelihood or professional work, as well as their household appliances;

ለ) ለተጠርጣሪው፣ ለተከሳሹ፣ ለፍርደኛው ወይም በስሩ ለሚተዳደሩ የቤተሰብ አባላት ለዕለት ኑሮ ጠቃሚ የሚሆኑ እና ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ በልዩ ሁኔታ ለሚወስነው ጊዜ የሚሆን ስንቅ፤

b) such amount of money or assets necessary for the daily life of the suspect, the accused or his family for a maximum of one year, or for a period determined by the Court on exceptional circumstances.

እንዳይታገድ ወይም እንዳይያዝ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠርጣሪው፣ ተከሳሹ፣ ፍርደኛው ወይም በስሩ ለሚተዳደሩ የቤተሰብ አባላት ሌላ ንብረት የሌላቸው ሲሆኑና የሚተዳደሩት ከተያዘው ወይም ከታገደው ንብረት በሚገኝ ገቢ ከሆነ ከታገደው ወይም ከተያዘው ንብረት ላይ መሠረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት ለተከሳሹና በእርሱ ስር ለሚተዳደሩ ጥገኞች ፍርድ ቤቱ በቂ ነው ብሎ የሚገምተውን ያክል ገቢ እየተቆረጠ እንዲከፈል ሊወስን ይችላል።

2/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Court may order for the payment of maintenance to suspect or accused or to the dependants of the suspect or the accused for their basic needs if they don't have any other income other than the asset that has been frozen or seized.

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሀ) የተደነገገው ድንጋጌ ቢኖርም በተለየ ሁኔታ ውድ ከሆኑ ማዕድናት ወይም ከፍተኛ ዋጋ ካላቸው የዕደጥበብ ስራዎች የተሰሩ ማናቸውም ቁሳቁሶች እንዲታገዱ ወይም እንዲያዙ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

፬/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ ወይም መርማሪ ፍርድ ቤት በሚያቀርበው በቂ ማስረጃ መሠረት ንብረቱ የወንጀል ፍሬ መሆኑን የሚያሳይ በሆነ ጊዜ ተጠርጣሪው፣ ተከሳሹ ወይም ፍርደኛው ከወንጀል ፍሬው የመጠቀም መብት አይኖረውም።

ክፍል አምስት

ስለ ንብረት መውረስ

፳፫. ጠቅላላ ድንጋጌ

፩/ ከወንጀል ድርጊት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተገናኘ ማንኛውም ንብረት፣ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ዝርዝር ድንጋጌዎች መሠረት ይወረሳል።

፪/ "በወንጀል ሕግ እና በሌሎች የወንጀል ድንጋጌዎች መሠረት የንብረት መወረስ እንደ ቅጣት ያልተቀመጠባቸው የወንጀል ድርጊቶች ቢኖሩም ማንኛውም ሰው በወንጀል ድርጊቱ የንብረት ጥቅም ስለማግኘቱ፣ ለሌላ ሰው ስለማስገኘቱ ወይም በሌላ ሰው የንብረት ጥቅም ላይ ጉዳት ስለማድረሱ ከተረጋገጠ በዚህ አዋጅ መሠረት የንብረት ማስመለስና መወረስ ሂደቱ ተፈፃሚ ይሆናል።

፫/ በዚህ አዋጅ ስለንብረት መውረስ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በወንጀል ድርጊቱ የንብረት ጥቅም ያገኘ፣ ያስገኘ ወይም ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው ያገኘውን ጥቅም በድርድር የሚመልስበትን ወይም ጉዳቱን የሚክስበትን ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፳፬. በንብረት መውረስ የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት

፩/ በአንድ የወንጀል ድርጊት የተሳተፉ ሰዎች የንብረት መውረስ ማመልከቻ የሚቀርብባቸው በሆነ ጊዜ ለደረሰው ጉዳት ወይም ለተገኘው

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) (a) of this Article the Court may give order of freezing or seizure on any assets made from precious metals, high value artisan souveniors and artifacts.

4/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article the suspect, the accused or his families may not have the right to use the assets where sufficient evidence is provided to the Court by the prosecutor or the investigator indicating that such assets are the proceed of crime.

PART FIVE

ASSET CONFISCATION

23. General Provisions

1/ An asset directly or indirectly related to a criminal act shall be confiscated based on the provisions provided in this Proclamation.

2/ Notwithstanding to the criminal code or other criminal provisions that do not provide asset confiscation as a punishment, any person who has obtained or procured for others an asset or causes damage to the assets of another due to a crime shall be subject to recovery and confiscation according to this proclamation.

3/ Without prejudice to asset confiscation provisions in this Proclamation, the condition of bargaining to recover an asset obtained for oneself or procured for others, or compensate the damage caused on another's asset shall be determined by a Directive issued by the Ministry.

24. Joint and Several Liability on Asset Confiscation

1/ When confiscation claim is brought against co-ofenders, confiscation of an asset will be sought from each of the

ያልተገባ ጥቅም ከእያንዳንዳቸው የሚወረስ ይሆናል::

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ከእያንዳንዳቸው ለማስመለስ በቂ ንብረት ለማግኘት ባልተቻለ ጊዜ የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት አለባቸው::

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) በተደነገገው መሠረት ንብረቱ የተወረሰበት ሰው ሊሎች የወንጀሉ ተሳታፊዎች ድርሻቸውን እንዲከፍሉ መጠየቅ ይችላል::

፳፭. ስለሚወረስ ንብረት

፩/ በጥፋተኝነት ላይ የተመሰረተ ወይም በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ የንብረት መውረስ ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት:-

ሀ) የወንጀሉ ፍሬ የሆነ ንብረት፣ የወንጀሉ ፍሬ ተቀላቅሎ ወይም ተለውጦ የተገኘ ንብረት፤

ለ) ከወንጀሉ ፍሬ የተገኘ ገቢና ሌሎች ጥቅሞችን የሚመለከት ንብረት፤

ሐ) ለወንጀሉ መፈፀሚያነት የዋለ ንብረት ወይም ከዚህ ንብረት የተገኘ ገቢ ወይም ትርፍ፤

መ) ባለቤትነቱ የተላለፈለት ሰው ቅን ልቦና እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከፊደል (ሀ) እስከ ፊደል (ሐ) የተጠቀሰውን ንብረት:-

(፩) ንብረቱን፤

(፪) የወንጀሉን ፍሬ ወይም ተመጣጣኙን፤

(፫) ተቀላቅሎ ወይም ተለውጦ የተገኘ ንብረትን፤

(፬) ከወንጀሉ ፍሬ የተገኘ ገቢን ወይም ለወንጀሉ መፈፀሚያነት የዋለ ንብረትን፤

ከመወረስ ለማዳን በማሰብ ለማንኛውም ወገን የተላለፈ ንብረት::

particpants for damage caused or undue advantage obtained.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, co-ofenders shall be jointly and severally liable when it is not possible to obtain sufficient asset to recover from each of them.

3/ If the asset is confiscated pursuant to Sub-Article (2) of this Article, the person whose asset has been confiscated shall have a right of subrogation to claim their share of liability from other perpetrators.

25. Assets Subject to Confiscation

1/ The Court to whom a conviction or non-conviction based confiscation claim brought shall issue an order of confisication as per the claim for the confiscation of :

a) assets constituting the proceeds of the crime, intermingled with or exchanged assets for such proceeds;

b) any income or other benefits obtained from the proceeds of the crime;

c) instrumentalities of a crime or any income or profit thereof;

d) without prejudice to the right of a third party in good faith, details listed from Paragraph a) to c) of Sub-Article (1) of this Article

(1) assets;

(2) proceeds of crime or its proportionate value;

(3) intermingled or exchanged assets;

(4) income from proceeds of crime or instrumentalities of the crime;

that are transferred to other parties in order to escape confiscation.

ሠ) ከወንጀሉ ፍሬ እንዲሁም ከዚሁ የወንጀል ፍሬ የተገኘ ገቢ፣ ከወንጀል ፍሬው ጋር ተቀላቅሎ ወይም ተለውጦ ከተገኘው ንብረት ወይም ለወንጀል መፈፀሚያነት ከዋለ ንብረት ጋር ተመጣጣኝ ግምት ያለው የወንጀል ፈፃሚው ንብረት፣

በቀረበለት ማመልከቻ መሠረት እንዲወረስ ይወስናል።

e) asset of the accused to the proportional values of the proceeds of the crime, income from the proceeds, intermingled or exchanged assets or instrumentalities of the crime.

፪/ እንዲወረስ ማመልከቻ በቀረበበት ወይም ውሳኔ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብት አለኝ በሚል ማመልከቻውን ወይም ውሳኔውን ለመቃወም ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው በንብረቱ ላይ መብት ሲተላለፍለት ምንጩ ሕገ-ወጥ መሆኑን ሳያውቅና ተገቢ የሆነ ዋጋ ከፍሎበት ወይም ለሰጠው ተመጣጣኝ አገልግሎት ታስቦለት መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የንብረቱን መወረስ ሊያስቀረው አይችልም።

2/ An application for confiscation or the Court's decision regarding confiscation, will not be accepted unless the contestant demonstrate to the Court's satisfaction that they were unaware of the unlawful origin of the asset and that they acquired it by paying a fair price at the time of transfer of the asset or providing services in proportion to its value.

፫/ ማንኛውም በወንጀል የተፈረደበት ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የያዘው እና በወንጀሉ ከመከሰሱ አስቀድሞ ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ የተገኘ ንብረት ጥፋተኛ የተሰኘበት ወንጀል ውጤት ነው ብሎ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ካለና ግለሰቡ በሕጋዊ መንገድ ያፈራው ስለመሆኑ በማስረጃ ማረጋገጥ ካልቻለ በተጨማሪነት እንዲወረስ ፍርድ ቤቱ ሊወስን ይችላል።

3/ The Court may also order confiscation of assets belonging directly or indirectly to a person convicted of a crime which were acquired during a period of five years prior to being charged with the offence, if there are reasonable grounds indicating that such assets are the results of the offence of which the person was convicted, and the person failed to prove that the asset was obtained legally.

፬/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት የንብረቱን መወረስ ለማስቀረት ዓላማ የተደረገ ማንኛውንም ሕጋዊ ሰነድ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ማድረግ ይችላል፣ ሆኖም ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የተደረገው ሰነድ የተፈረመው ዋጋ በተከፈለበት ግንኙነት ላይ ተመስርቶ ከሆነ በቅን ልቦና ክፍያ የፈፀመው ተዋዋይ ወገን የከፈለው ገንዘብ ብቻ ከሚወረሰው ንብረት ላይ ተመላሽ ይደረግለታል።

4/ The Court may invalidate any legal instruments, the purpose of which is to avoid the confiscation of any property pursuant to Sub-Article (2) of this Article; provided however, that if the invalidated legal instrument is entered into for the value, the acquired party acting in good faith shall be reimbursed only for the amount actually paid from confiscated asset.

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሠ) መሠረት ከወንጀል ፍሬው ጋር ተቀላቅሎ የሚገኝ ንብረት የሚወረሰው ተቀላቅሎ በተገኘው መጠን ብቻ ይሆናል።

5/ As per Sub-Article (1) (e) of this Article where proceeds of crime is an intermingled asset, the asset to be confiscated shall be equal to the value of the intermingled asset.

፮/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፭) ድንጋጌ ቢኖርም ከወንጀል ፍሬው ጋር ተቀላቅሎ የሚገኝ ንብረት በሚከተሉት ሁኔታዎች ሙሉ ለሙሉ እንዲወረስ ፍርድ ቤቱ ሊወሰን ይችላል፡-

ሀ) በወንጀል የተገኘው ንብረት ለሕጋዊው ንብረት ዓይነተኛ ሚና ያለው ሲሆን ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ለንብረቱ ዋና ክፍል ሲሆን፤ ወይም

ለ) በወንጀል የተገኘውን ንብረቱን ሕጋዊ ለማስመሰል የተጠቀመበት እንደሆነ፡፡

6/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (5) of this Article the ourt may decide the consification of the total intermingled assets where;

a) the value of the proceed of the crime is of Classic to the legal asset or has a substantial or functional role to the legal asset; or

b) the legal asset is used to launder the proceeds of the crime.

፳፮. ንብረት ለማስወረስ ማመልከቻ በድጋሚ ስለማቅረብ

26 Reapplication for Asset Confiscation

፩/ የንብረት ማስወረስ ማመልከቻ በቀረበበት ተከሳሽ ላይ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ወይም ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ማንኛውም ከወንጀል ድርጊቱ ጋር የሚገናኝ ንብረት የተገኘ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ አዲስ የተገኘውን ንብረት በተመለከተ አዲስ የንብረት ማስወረስ ማመልከቻ ያቀርባል፡፡

1/ When a new asset is identified that relates to the crime before or after a final confiscation decision is delivered by the Court, the prosecutor could bring a new confiscation application on the newly identified asset.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ስር በተደነገገው መሠረት ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት አዲስ የተገኘው ንብረት የመጀመሪያው ማመልከቻ ሲቀርብ አብሮ ለማቅረብ የሚያስችል ማስረጃ ባለመኖሩ ወይም በማናቸውም በቂ ምክንያት መሆኑን ሲያረጋግጥ ማመልከቻውን ይቀበላል፡፡

2/ Pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the Court to which the application is made shall accept the application when it confirms that there was no prior evidence on the newly identified asset during the first application was made or for any other sufficient reason.

፳፯.ከክስ ነፃ የሚደረግ ምስክር ንብረትን ስለማስመለስ

27. Asset Recovery of Exempted Witnesses

፩/ በሌሎች ሕጎች በሚወጡ ድንጋጌዎች መሠረት ከክስ ነፃ የሚደረግ እና በወንጀል ክርክር ሂደቱ ወደ ምስክር የዞረ የወንጀል ተካፋይ የሆነ ሰው በወንጀል ድርጊቱ ያገኘውን ንብረት እንዲመልስ ወይም ያደረሰውን ጉዳት እንዲክስ ይደረጋል፡፡

1/ Whoever is exempted from prosecution and turned in to a witness pursuant to provisions of other laws shall return any assets obtained from the crime of his participation or shall compensate the damage.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የወንጀል ጥፋተኝነት ድርድር ላይ የሚደረጉ ስምምነቶችን አይመለከትም፡፡

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the exemption shall not apply to plea bargaining agreements.

፳፰. በውርስ ላይ ይግባኝ ስለማቅረብ

28. Appeal on Confiscation

፩/ ፍርድ ቤት በሚሰጠው የንብረት መውረስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ለሚመለከተው የበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

1/ Anyone aggrieved by the decision of the Court on confiscation have the right to appeal to the relevant Higher Court.

፪/ ፍርድ ቤቱ የታገደው ወይም የተያዘው ንብረት እንዳይወረስ በሚል የወሰነ እንደሆነ እና ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ የቀረበ እንደሆነ አስቀድሞ የተሰጠው የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ ይግባኙ ወይም አቤቱታው የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ፀንቶ ይቆያል።

2/ If the Court decides not to confiscate the asset that has been frozen or seized and an appeal or petition for cassation has been filed against this decision, the freezing or seizure order will remain in force until a final decision is given to the appeal or petition.

፫/ ፍርድ ቤቱ የታገደው ወይም የተያዘው ንብረት እንዳይወረስ የወሰነ እንደሆን ዐቃቤ ሕጉ ይግባኝ መጠየቁን የሚያስረዳ የጽሁፍ ማስረጃ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ከይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ካላመጣ በስተቀር ንብረቱ እንዲለቀቅ ይወስናል።

3/ If the Court decides not to confiscate the asset that has been frozen or seized, the decesion may stand unless the prosecutor submitts a written evidence about the appeal with in fifteen days from the Appellate Court.

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሠረት የተቀመጠው የአስራ አምስት ቀን የጊዜ ገደብ የሚቆጠረው ዐቃቤ ሕግ የውሳኔው ግለባጭ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ነው።

4/ The fifteen days' time limit pursuant to Sub-Article (3) of this Article shall be counted after the day when the public prosecutor receives the copy of the Court decision.

፳፱. <u>በጥፋተኝነት ላይ የተመሰረተ የንብረት መውረስ</u>

29. <u>Conviction Based Confiscation</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በወንጀል ክስ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ እና ከወንጀል ድርጊቱ የንብረት ጥቅም ያገኘ፣ ለሌላ ሰው ያስገኘ ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት ንብረት እንዲወረስ ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ያቀርባል።

1/ Whoever is convicted for a crime by the Court and obtains assets from such crime, procure benefits for others or injure the interest of another person, the prosecutor shall make an application to the Court for the confiscation of the asset in accordance with this Proclamation.

፪/ የወንጀል ቅጣቱ በይቅርታ ወይም በምህረት ቀሪ የተደረገለት፣ የተገደበለት ወይም በአመክሮ የተለቀቀ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ለሚቀርብ የንብረት ማስመለስ ሂደት መቃወሚያ አድርጎ ማቅረብ አይችልም።

2/ Any sentenced person who has been granted a pardon or amenesty, whose penality is suspended or released on parol cannot object to an asset recovery claim brought against him pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

፫/ ጥፋተኛ በተባለ ሰው ላይ የንብረት መውረስ ማመልከቻ የሚቀርበው ለወንጀል ቅጣት አፈፃፀም በወንጀል ሕግ ወይም በሌሎች የወንጀል ድንጋጌዎች በተቀመጠው የይርጋ የጊዜ ገደብ መሠረት ይሆናል።

3/ The period of limitation for the application of asset confiscation against the convicted person shall take the period set by the criminal law or other criminal law provisions for the execution of the penalty.

፬/ ዐቃቤ ሕግ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ በቀረበለት ማመልከቻ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ባለው ማንኛውም ጊዜ ፍርድ ቤቱን በማስፈቀድ ማመልከቻውን ለማሻሻል ይችላል።

4/ Upon the approval of the Court, the prosecutor can amend the asset confiscation application at any time before a final decision is given by the Court.

፴. በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ የንብረት መውረስ

፩/ ማንኛውም ሰው በወንጀል ክስ የጥፋተኝነት ውሳኔ ባይሰጥበትም ከድርጊቱ የንብረት ጥቅም ያገኘ ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት ንብረት እንዲወረስ ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ያቀርባል።

፪/ በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ የንብረት መውረስ ማመልከቻ የሚቀርበው ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ ቢያንስ አንዱ በተሟላ ጊዜ ነው፡-

ሀ) በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረው ወይም የተከሰሰው ሰው ሲሞት፣ ሲያመልጥ፣ ሲጠፋ ወይም ወንጀል ፈፃሚው ሳይታወቅ ሲቀር፤

ለ) በይርጋ ምክንያት የወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔ ማሰጠት ሳይቻል ሲቀር፤

ሐ) የተገኘው ማስረጃ በወንጀል ክስ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለማሰጠት የወንጀል የማስረጃ ምዘና መስፈርትን የማያሟላ መሆኑ ተከሳሹን ከንብረት መውረስ ክስ ነፃ አያደርገውም፤

መ) በወንጀል ምርመራ ሂደት የተገኘው ማስረጃ ለወንጀል ሥነ-ሥርዓት ተቀባይነት የሌለው ሲሆን ወይም በዚህ ምክንያት ተከሳሹ ከቀረበበት የወንጀል ክስ ነፃ የተባለ እንደሆነ፤

ሠ) ተከሳሹ ምህረት ሲደረግለት ወይም የቀረበበት ክስ በማንኛውም ምክንያት ሲቋረጥ፤

ረ) የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠበት የወንጀል ድርጊት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚገናኝ እና በሶስተኛ ወገን ይዞታ ወይም ባለቤትነት ስር የሚገኝ ንብረት ሲሆን፤

ሰ) ተጠርጣሪው በወንጀል ያለመከሰስ መብት ያለው ሲሆን፤

ሸ) በአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተጠቀሱ ተቋማትን ሳይጨምር የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ተቋማት ከወንጀል ድርጊታቸው ንብረት ያገኙ ሲሆን እና በወንጀል የማይከሰሱበት ሁኔታ ሲኖር፤

30. Non-Conviction Based Confiscation

1/ Whoever is not convicted of a crime but obtains assets from such act, the prosecutor shall apply to the Court for non-conviction-based confiscation pursuant to this Proclamation.

2/ Application for non-conviction-based confiscation shall be made to the Court upon the fulfillment of any of the following conditions, when:

a) the suspect or the accused dies, absconds, or unavailable by the reason of flight, or when the perpetrator remains unknown;

b) a conviction could not be obtained due to period of limitation;

c) there is reasonable suspicion to establish that the proceeds were generated from a criminal activity but the evidence is not sufficient to meet the crimie evidence standard to entail conviction;

d) The evidence collected against the accused at the time of investigation is inadmissible or because of this the accused is acquitted from the crime;

e) the charges against the accused is discontinued due to amnesty or for any other reasons;

f) the asset to be confiscated is under the ownership or possession of the third party but directly or indirectly related with the person convicted for the crime;

g) the suspect has the right to immunity from prosecution;

h) Except institutions listed under Article 4(2) of this Proclamation, a legal person that has acquired an asset from a criminal act, and cannot be charged for the crime;

ቀ) ከክስ ነፃ ተደርጎ ወደ ምስክርነት የዞረ እና በድርጊቱ ያገኘውን ንብረት ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ሲያጋጥም::

ክፍል ስድስት
ስለ ንብረት ማስተዳደር

፴፩. ንብረት አስተዳዳሪ ስለመሾም

ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት፣ በዐቃቤ ሕግ፣ በመርማሪ ፣ በተጠርጣሪው ወይም በንብረቱ ላይ መብት አለኝ በሚል ሶስተኛ ወገን ጠያቂነት በዚህ ሕግ መሠረት የተያዘ ንብረት በንብረት አስተዳዳሪ ስር እንዲቆይ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የንብረት አስተዳደር መሾም ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን የንብረት አስተዳደር እንዲሾም ለማዘዝ ይችላል::

፴፪. ንብረት አስተዳዳሪ ስለሚመረጥበት ሁኔታ

፩/ ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ሰው የንብረት አስተዳዳሪ ሆኖ ሊሾም ይችላል::

፪/ ፍርድ ቤት የንብረት አስተዳዳሪ ሲሾም በማናቸውም ሁኔታ የጥቅም ግጭት የሌለ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት::

፫/ ፍርድ ቤቱ የንብረት አስተዳዳሪ በሚሾምበት ሂደት የዐቃቤ ሕግን እና የሚቻል በሆነ ጊዜ የንብረቱን ባለመብቶች አስተያየት መስማት አለበት::

፴፫. የንብረት አስተዳዳሪው ተግባርና ኃላፊነት

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተያዘ ንብረትን እንዲያስተዳድር የተሾመ ማንኛውም ሰው:-

ሀ) እንደንብረቱ ዓይነትና ሁኔታ በሕግ አግባብ የንብረቱን ኢኮኖሚያዊ ወይም ሌላ ጥቅም በተሻለ ለመጠበቅ ምክንያታዊ እና ተገቢ የሆነ ማንኛውንም የአስተዳደር ሥራ ይሰራል፤

ለ) በአስተዳዳሪነት የተሾመበትን ንብረት በተመለከተ የመክሰስ እና የመከሰስ መብት ይኖረዋል፤

i) a person who has been exempted from prosecution and turned into a witness is not willing to return the proceeds of the crime.

PART SIX
ASSET MANAGEMENT

31. Appointment of Asset Manager

Upon the initiation of the Court, the prosecutor, the suspect or third party with vested interest can brought an application for the appointment of an asset manager and the Court shall give such order when it deems necessary.

32. Condition for Appointment of Asset Manager

1/ Any natural or legal person could be appointed as an asset manager.

2/ While appointing the asset manager, the Court shall ensure the absence of conflict of interest.

3/ Upon appointment of the asset manager, the Court shall hear opinion of the public prosecutor and whenever possible, the property rights holders.

33. Duties and Functions of the Asset Manager

1/ Any asset manager appointed by the Court under this Proclamation shall:

a) carryout all the appropriate and reasonable management works depending on the nature of the asset in order to keep the economic and other values of the asset according to the law;

b) have the right to sue or be sued in a Court of law in relation to the asset appointed to manage;

ሐ) ከንብረቱ የሚገኝ ኪራይ፣ ትርፍ ወይም ሌላ ማንኛውንም ገቢ ይሰበስባል፤

መ) ንብረት አስተዳዳሪው ንብረቱን መያዣ ከማድረግ እና ወደ ሶስተኛ ወገኖች ከማስተላለፍ በስተቀር የንብረት ባለመብት በሕግ ዕውቅና የተሰጠው ሥልጣኖች ይኖሩታል፤

ሠ) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) (መ) ድንጋጌ ቢኖርም የተያዘውን ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል መያዣ ለማድረግ ወይም ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ይህንኑ ተግባር የመፈፀም ሥልጣን እንዲሰጠው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሠ) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻን ወይም በአንቀፅ ፴፬(፬) መሠረት የሚቀርብ ሪፖርትን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግን እና የሚቻል በሆነ ጊዜ የንብረቱን ባለመብት አስተያየት ከሰማ በኋላ ጥያቄውን በመቀበል እንዲፈፀም ለማዘዝ፣ ለማሻሻል ወይም ውድቅ ለማድረግ ይችላል።

፫/ የመንግስትም ሆነ የግል ተቋም ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ንብረት ለማስተዳደር ሥልጣን ለተሰጠው የንብረት አስተዳዳሪ የስራ ግዴታውን ለመወጣት አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የመተባበር ግዴታ አለበት።

፴፬. የንብረት አስተዳዳሪው ግዴታዎች

በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፩ መሠረት የሚሾም ንብረት አስተዳዳሪ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

፩/ እንዲያስተዳድር የተሾመበትን ንብረት በተመለከተ ኃላፊ ለመሆን የሚችል ዋስ ወይም መያዣ የመስጠት፤

፪/ ፍርድ ቤቱ በሚወስነው መሠረት ከንብረት ማስተዳደር የሚገኘውን ትርፍ ገቢ ማድረግ፤

፫/ በራሱ ከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ ባደረገው ጉድለት በተረከበው ንብረት ላይ ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነት የመውሰድ፤

c) collect rents, profits, or any other income thereof;

d) have all the powers that an owner has except to use the assets for mortgage or transfer to third parties;

e) Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) (d) of this Article, when he believes necessary to use the asset as a mortgage either partially or in full or transfer such assets to third parties, such request shall be submitted to the Court for approval.

2/ When a request is made in accordance with Sub-Article 1 (e) of this Article or a report is submitted as per Article 34 (4) of this Proclamation, the Court after hearing 0f opinion of the public prosecutor and whenever possible the property rights holders, shall determine whether to accept, amend, or dismiss the application.

3/ In matters essential for the proper execution of asset management duties, any government institution, private organization, or individual has an obligation to cooperate with the asset manager.

34. The Duties of the Asset Manager

An asset manager who is appointed as per Article 31 of this Proclamation shall have the following duties:

1/ to furnish a security or surety to be responsible for the asset he is appointed to manage;

2/ to handover the required income generated from the asset managemnt as determined by the Court;

3/ to take responsibility and pay for any damage caused to the asset due to his own gross negligence or intentional misconduct;

፬/ ስለንብረቱ አያያዝ እና ስለተወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም ስለአጠቃላይ ሁኔታዎች ለፍርድ ቤት በየሶስት ወሩ የሂሳብ መግለጫ እና ሪፖርት የማቅረብ።

4/ submit financial and other report to the Court every three months about the management of the asset and every measure taken in the process.

፴፭. ስለ ንብረት አስተዳዳሪው ክፍያ

35. Remuneration for the Asset Manager

፩/ ፍርድ ቤቱ ለንብረት አስተዳዳሪው ከሚወረሰው ንብረት ላይ የሚከፈለውን የአገልግሎት ክፍያ ይወስናል።

1/ The Court shall determine the remuneration of the asset manager from the confiscated asset.

፪/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አገልግሎት ክፍያውን በመወሰን ሂደት የንብረቱን ባህሪ፣ የአስተዳደር ስራውን ክብደት፣ ለሥራው የሚያስፈልገውን የካፒታል መጠን፣ የሥራውን ውጤታማነት እና ሌሎች ምክንያቶችን ከግምት በማስገባት የንብረት አስተዳዳሪውን፣ የዐቃቤ ሕግን እና የሚቻል በሆነ ጊዜ የንብረቱ ባለቤት ወይም ባለመብት አስተያየት በመስማት ይሆናል።

2/ The Court shall consider the nature of the work,the complexity of the management tasks, the required capital, the success achieved in the work, and other relevant factors when determining the remuneration for the asset manager in accordance with Sub-Article (1) of this Article. In doing so, the Court shall consider the opinions of the asset manager, the prosecutor, and, whenever feasible, the input of the asset owner.

፴፮. ንብረት ማስተዳደርን በተመለከተ የዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት

36. The Responsibilities of the Prosecutor in Asset Management

፩/ ዐቃቤ ሕግ ንብረት ማስተዳደርን በተመለከተ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1/ The public prosecutor shall have the following responsibilities in the asset management process:

ሀ) የንብረት አስተዳዳሪ እንዲሾም ወይም እንዲሻር ማመልከቻ የማቅረብ፤

a) apply for the appointment or revocation of the asset manager;

ለ) የሚያዘውን ንብረት ከሶስተኛ ወገን ነፃ በማድረግ ለንብረት አስተዳዳሪው የማስረከብ፤

b. free the asset from the third party and hands it over to the asset manager;

ሐ/ የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ የተሰጠበት ማንኛውንም ዓይነት ንብረት በተመለከተ መደበኛ የጉብኝትና ቁጥጥር ስራ የመስራት።

c. conduct regular supervision and regulation of the asset for which a freezing or seizure order has been issued.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሐ) የተደነገገው ድንጋጌ ቢኖርም እንደየአስፈላጊነቱ ዐቃቤ ሕግ ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት እስከ ምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ባለው ጊዜ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ ሳያስፈልገው ድንገተኛ ጉብኝት እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይችላል።

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) (c) of this Article, when necessary, the prosecutor may conduct unexpected supervision and regulation without a Court warrant between 6 AM to 6 PM.

፫/ ዐቃቤ ሕግ በሚያደርገው መደበኛም ሆነ ድንገተኛ ጉብኝት የሚያገኘው ጉድለት በተመለከተ ለአስተዳዳሪው እርማት ከማድረግ ጀምሮ አስተዳዳሪ እንዲቀየር የሚጠይቅ ማመልከቻ ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

3/ based on amiss following a regular or surprise visit, the prosecutor can ask for the replacement of the manager or for the taking of corrective measures.

፴፯. <u>የተወረሰ ንብረት አጠቃቀም</u>

፩/ የገንዘብ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ከተወረሰ ንብረት ሽያጭ የሚገኝ ገንዘብ የሚቀመጥበት የባንክ ሂሳብ ይከፍታል::

፪/ የሚወረሰውን ገንዘብ ወይም ንብረትን በተመለከተ ተጎጂ ሲኖር ከወንጀል የተገኘው ንብረት በዓይነት በተገኘ ጊዜ ለተጎጂው የሚመለስ ሲሆን ተለውጦ፣ ተላልፎ ወይም ተቀላቅሎ በተገኘ ጊዜ የደረሰው ጉዳት ትክክለኛ ዋጋ በብር ይከፈለዋል::

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ለተጎጂው የሚመለሰው ንብረት እንደተጠበቀ ሆኖ ለተጎጂው ከሚከፈለው ንብረት የሚተርፍ ንብረት ይወረሳል::

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተወረሰ ንብረት በቀጥታ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በማድረግ የፍትህ ሥርዓቱን ለማሻሻል ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል::

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) መሠረት ለፍትህ ሥርዓቱ ማጠናከሪያ የሚውለው ንብረት አጠቃቀም በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል::

፮/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የሽብር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እና በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ መሠረት የተቋቋመው የተጎጅዎች ፈንድን የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው::

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>ስለ ንብረት ማስመለስ ዓለም አቀፍ ትብብር</u>

፴፰. <u>ጠቅላላ</u>

፩/ ሚኒስቴሩ ለዚህ አዋጅ ዓላማ ሲባል የዓለም አቀፍ የትብብር ማዕከላዊ ባለስልጣን ነው::

37. <u>Utilization of Confiscated Asset</u>

1/ The Ministry of Finance shall open a bank account for the deposit from the sale of confiscated assets under the provisions of this Proclamation.

2/ When there is a victim of asset confiscated, the asset obtained from the crime will be returned to the victim when it is found in kind, and when it is found to be changed, transferred or intermingled, the actual value of the damage will be paid in cash.

3/ Without prejudice the asset to be returned to the victim as per Sub-Article (2) of this Article, all the remaining assets shall be confiscated.

4/ An asset confiscated in kind or cash deposited in Bank as per Sub-Article (1) of this Article shall be hall be directly transferred to government treasury and used to enhance the justice system.

5/ Council of Ministers shall issue a Regulation about utilization of the assets to be used for the justice administration institution as per Sub-Article (4) of this Article.

6/ Notwithstanding the provision of this Proclamation, the victims fund provisions established pursuant to the Prevention and Suppression of Trafficking in Persons, Smuggling of Persons and Prevention, and Suppression of Terrorism Crimes Proclamations shall remain in force.

<u>PART SEVEN</u>

<u>International Cooperation on Asset Recovery</u>

38. <u>General Provisions</u>

1/ For the purpose of this Proclamation, the Ministry shall be the Central Authority on International Cooperation.

፪/ ንብረት ማስመለስን በሚመለከት በጋራ ወይም በተናጠል ምርመራ የማድረግ፣ ንብረቶችን የመያዝ ወይም የማገድ፣ ለማስተዳደር፣ በጥፋተኝነት ላይ የተመሰረተ ወይም በጥፋተኝነት ላይ ባልተመሰረተ ንብረት ለመውረስ፣ ለማስመለስና ለፍርድ በማቅረብ ረገድ ከሌሎች ሃገሮች አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት ለሚቀርብ የትብብር ጥያቄ ሚኒስቴሩ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት የጋራ የሕግ ድጋፍ ትብብር ማድረግ አለባቸው፡፡

2/ The Ministry and other Competent Authorities shall provide cooperation to the request made by competent authority of other states, for the purposes of mutual legal assistance in connection with asset recovery, joint investigation, freezing or seizure, conviction bases and non-conviction bases confiscation, asset management and repatriation.

፴፱. <u>የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ</u>

39. <u>Requests for Mutual Legal Assistance</u>

፩/ የንብረት ማስመለስን በሚመለከት የጋራ የሕግ ድጋፍ ጥያቄ በሌላ ሃገር አመልካችነት ሲቀርብ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ይስተናገዳል፡፡

1/ Upon application by a foreign state, requests for mutual legal assistance on asset recovery shall be executed in accordance with provisions of this part.

፪/ የንብረት ማስመለስን በተመለከተ የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

2/ Mutual legal assistance request regarding asset recovery may include:

ሀ) ንብረቱን በተመለከተ ከሰዎች ማስረጃ ወይም ቃል መቀበልን፤

a) taking evidence or statement from persons regarding the asset;

ለ) የተያዙ ሰዎችን ወይም ፍቃደኛ የሆኑ ምስክሮችን ማስረጃ እንዲሰጡ ወይም ምርመራውን እንዲረዱ ለጠያቂው አገር የዳኝነት አካላት ማቅረብን፤

b) assisting in making detained persons or voluntary witnesses available to the judicial authority of the requesting state in order to give evidence or assist in investigation;

ሐ) የፍርድ ቤት ሰነዶችን ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ማድረግ፤

c) effecting service of judicial documents to relevant bodies;

መ) የፍተሻ፣ የመያዝ ወይም የማገድ ሌሎች ጊዜያዊ እርምጃዎችን ማስፈፀም፤

d) executing searches, seizure, freezing or other temporary measures orders;

ሠ) መረጃዎችን፣ የማስረጃ ቁሳቁሶችንና የባለሙያ ግምቶችን መስጠት፤

e) providing information, evidentiary items and expert evaluation;

ረ) የመንግስት፣ የባንክና የፋይናንስ፣ የተቋማት ወይም የንግድ ስራ መዝገቦችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችንና መዝገቦችን ዋና ወይም የተረጋገጡ ቅጅዎችን መስጠት፤

f) providing original or certified copies of relevant documents and records including government, bank, financial, institutions or business records;

ሰ) የወንጀል ፍሬን፣ የወንጀል መፈፀሚያዎችን፣ ለወንጀል መፈፀሚያነት ለመዋል የታሰበ ንብረት፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ንብረት ወይም ሌሎች ነገሮችን ለማስረጃነት ወይም ለመውረስ ዓላማ ተከታትሎ መለየትን ወይም ማግኘትን፣

g) identifying or tracing the proceeds of crime, instrumentalities, instrumentalities enteded to use, property of corresponding value or other things for evidentiary or confiscation purposes;

ሸ) ንብረት መውረስን ወይም ማስመለስን፤

ቀ) ሌሎች ከኢትዮጵያ ሕጎች ጋር የማይቃረኑ የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄዎችን።

h) confiscation or recovery of assets;

i) any other forms of mutual legal assistance not contrary to the laws of Ethiopia.

፵. የምርመራ ስራን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ

፩/ አግባብነት ያለው የጠያቂው አገር ባለስልጣን በኢትዮጵያ ሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ጋር የማይቃረን ለየት ያለ ሥርዓት ተከትሎ እንዲፈፀም ካልተጠየቀ በስተቀር ምርመራው የሚካሄደው በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገገውን የሕግ ሥርዓት ተከትሎ ነው።

፪/ የጠያቂው አገር አግባብ ያለው ባለስልጣን የመደበው የመንግስት ኃላፊ የምርመራ ሥራውን አፈፃፀም እንዲታዘብ ሊፈቅድለት ይችላል።

40. Requests for Investigative Measures

1/ Investigative measures shall be undertaken in conformity with the procedural rules of Ethiopia unless the competent authority of the requesting state requested a specific procedure not contrary to such rules.

2/ A public official authorized by the competent authority of the requesting state may be allowed to attend the execution of the investigative measures.

፵፩. ጊዜያዊ እርምጃዎች መውሰድን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ

፩/ በጠያቂው አገር እንዲወሰዱ የተጠየቁ ጊዜያዊ እርምጃዎች አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሚፈፀሙ ሲሆን እንዲወሰዱ የተጠየቁት እርምጃዎች በጥቅል አነጋገር የተገለፁ ከሆነ እና በሕጉ የተደነገጉትና ይበልጥ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

፪/ የተጠየቁ እርምጃዎች በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገጉ ካልሆኑ አግባብ ያለው ባለስልጣን በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገጉት እና በውጤት ይበልጥ ቅርበት ያላቸው እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል።

፫/ ጊዜያዊ እርምጃዎችን ስለማንሳት በዚህ አዋጅ የተደነገገው ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፤ ሆኖም እርምጃዎቹ እንዲነሱ ከመደረጋቸው በፊት አግባብ ያለው የጠያቂው አገር ባለስልጣን እንዲያውቀው ይደረጋል።

41. Request for Provisional Measures

1/ Provisional measures requested by the requesting state shall be undertaken in accordance with the applicable laws of Ethiopia and if the request is worded in general terms, the most appropriate measures provided by law shall be used.

2/ Where the applicable laws of Ethiopia do not provide for the measures requested, the competent authority may substitute those measures provided for in law whose effects correspond most closely to the requested measures.

3/ The provisions relating to the lifting of temporary measures as lied down of this Proclamation shall be applicable; provided, however, that before lifting the provisional measures applied, the competent authority of the requesting state shall be informed thereof.

፵፪. የመውረስ እርምጃን የሚመለከት ድጋፍ ጥያቄ

፩/ የንብረት መውረስ ትዕዛዝ እንዲፈፀም የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብ ሚኒስቴሩ በጠያቂው አገር ፍርድ ቤት ለተሰጠው ውሳኔ እውቅና ሰጥቶ ማስፈፀም ወይም በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የመውረስ ትዕዛዝን እውቅና በማሰጠት ጉዳዩን ማስፈፀም አለበት።

42. Request for Confiscation

1/ In the case of a request for mutual legal assistance seeking the execution of a confiscation order, the Ministry shall either recognize and enforce the confiscation order made by the Court of the requesting state or shall submit the request to the Court for the purpose of

፪/ በጠያቂው ሃገር ፍርድ ቤት ለተሰጠው የመውረሻ ትዕዛዝ እውቅና ተሰጥቶ የሚያስፈፅም ከሆነ ትዕዛዙ የተመሰረተበትን የማስረጃ ግኝቶች እንዳለ ወስዶ ማስፈፀም አለበት፡፡

፫/ የንብረት መውረስ ትዕዛዙ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚሸፈን እና በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ንብረትን የሚመለከት መሆን አለበት፡፡

፵፫. የመገናኛ ቋንቋ

፩/ የሕግ ድጋፍ ትብብር ጥያቄ እንዲሁም ደጋፊ ሰነዶች በጽሁፍ ተደርገው በፌደራል ቋንቋ መቅረብ አለባቸው፡፡

፪/ አስቸኳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሕግ የጋራ ድጋፍ ትብብር ጥያቄ በቃል ሊቀርብ ይችላል፣ ሆኖም ግን አስፈላጊ ነገሮችን የሚያሟላ የጽሁፍ ጥያቄው በአስር ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

፵፬. ከአንድ በላይ በሆኑ ሃገሮች የጋራ ትብብር ድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብ

በተመሳሳይ ንብረት ላይ የጋራ የሕግ ድጋፍ ጥያቄ ከአንድ በላይ በሆኑ አገሮች ሲቀርብ በመጀመሪያ የሁለትዮሽ ስምምነት ያላቸው አገራት፣ በመቀጠል በዓለም አቀፍ የጋራ ስምምነት መሠረት በመቀጠል የእንካ ለእንካ ስምምነት ያላቸውን ሃገሮች ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

፵፭. በሕግ የጋራ ድጋፍ ትብብር ስለሚወጣ ወጪ

፩/ በስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር የትብብር ወጪ በትብብር ጠያቂ ሃገር የሚሸፈን ይሆናል፡፡

፪/ በኢትዮጵያ የሚጠየቅ ትብብር ወጭው በፌደራል መንግስት ይሸፈናል፡፡

፫/ በኢትዮጵያ የሚሸፈን የትብብር ወጪ ክፍያ በፌደራል መንግስት የገንዘብ ሥርዓት እና የፋይናንስ ሕግ መሠረት ይወሰናል፡፡

getting recognition of a confiscation order and if such order is granted, enforce it.

2/ Where the department recognizes and enforces a confiscation order issued by the Court of the requesting state, it shall be bound by the findings of fact on which the order is based.

3/ The confiscation order shall apply to assets referred to in this Proclamation and situated in the territory of Ethiopia.

43. Language of Communication

1/ Request for mutual legal assistance and supporting documents shall be in writing and in federal languages.

2/ In case of urgent matters, mutual legal assistance requests may be submitted orally but a request that fulfills all the requirements shall be submitted in writing within ten days.

44. Mutual Assistance Request by Multiple Countries

When a mutual legal assistance request is submitted by more than one country on a particular asset, priority shall be given to countries with bilateral agreement, international cooperation and principle of reciprocity respectively.

45. Costs for Mutual Legal Assistance

1/ Unless otherwise agreed, the cost of cooperation will be covered by the country requesting cooperation.

2/ The cost of cooperation requested by Ethiopia will be covered by the federal government.

3/ The cost of cooperation which is covered by Ethiopia shall be determined according to the federal government's financial law and system.

፵፮. የሕግ የጋራ ድጋፍ ጥያቄን ስለመከልከል

፩/ የሕግ የጋራ ድጋፍ ትብብር ጥያቄ በሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊከለከል ይችላል፡-

ሀ) የቀረበው ጥያቄ በዚህ አዋጅ ወይም ሌሎች አግባብነት ባለቸው የሃገሪቱ ሕጎች መሠረት ያልቀረበ ከሆነ፤

ለ) የቀረበውን የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ ማስፈፀም የኢትዮጵያን ሕግና ሥርዓት፣ ሉዓላዊነት፣ ደህንነት፣ የህዝብ ጥቅም፣ ሞራል ወይም ሌሎች መሠረታዊ ጥቅሞችን የሚነካ ከሆነ፤

ሐ) ጥያቄው የቀረበበት የወንጀል ድርጊት በኢትዮጵያ ውስጥ በመዳኘት ላይ ከሆነ ወይም የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፤

መ) የትብብር ጥያቄው የቀረበው በግለሰቡ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ዜግነት፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ ወይም ፆታ ላይ ብቻ ተመስርቶ መሆኑን ለማመን የሚያስችል ተጨባጭ ምክንያት ሲኖር፤

ሠ) በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተጠቀሰውን ወንጀል በሚመለከት የተጠየቀውን እርምጃ ወይም ተመሳሳይ ውጤት የሚኖረውን ሌላ እርምጃ መውሰድ የማይፈቀድ ከሆነ፤

ረ) በውጭ ሃገር የተሰጠው ውሳኔ የተከሳሹን የመከላከል መብት በበቂ ደረጃ ባላስተናገደ ሁኔታ የተሰጠ ከሆነ፤

ሰ) ትብብር የተጠየቀበት ንብረት እጅግ አነስተኛ ግምት የሚሰጠው ሲሆን።

፪/ ሚኒስቴሩ የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረበትን ምክንያት አግባብ ላለው የጠያቂው አገር ባለስልጣን ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

፵፯. ንብረቱን ስለማስወገድ ወይም ለጠያቂው አካል ስለመመለስ

፩/ በጠያቂው አገር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ መሠረት የተወረሰ ንብረት በሚከተለው መልኩ ሊወገድ ወይም ወደ ጠያቂው አካል ሊመለስ ይችላል፡-

46. Refusal to Mutual Assistance Requests

1/ A request for mutual legal assistance may be refused if:

a) the request is not made in accordance with this Proclamation or other appropriate laws of the country;

b) its execution is likely to prejudice the law and order, sovereignty, security, public interest, moral or other essential interests of Ethiopia;

c) the offense to which it relates is the subject of criminal proceedings or has already been the subject of a final judgment in the territory of Ethiopia;

d) there are substantial grounds for believing that the request is directed solely on account of the individual's race, religion, nationality, political opinion or gender;

e) under the legislation of Ethiopia, the measures requested or any other measures having similar effects, are not permitted with respect to the offences referred to in the request;

f) the decision rendered abroad was issued under conditions that did not afford sufficient protection with respect to the rights of the defendant;

g) the request for cooperation is based on an inconsiderate amount of assets.

2/ The Ministry shall promptly inform the competent authority of the requesting state about the grounds for refusal to execute the request.

47. Disposal or Repatriation of Assets

1/ The asset may be disposed or returned to the mutual legal assistance requesting authority on the following grounds:

ሀ) ከጠያቂው አካል ጋር በሚደረግ የሁለትዮሽ ስምምነት ወይም በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት፤

ለ) የሁለትዮሽ ስምምነትም ሆነ የዓለም አቀፍ ስምምነት በሌለ ጊዜ ከጠያቂው አገር ጋር እንደየጉዳዩ በሚደረግ ስምምነት።

፪/ የሚመለሰውን ንብረት በተመለከተ በተቀናጀና በጋራ የንብረት ማስመለሱን ያከናወኑ ከሆነ ንብረቱን የሚካፈሉበትን ሁኔታ በተመለከተ ሚኒስቴሩ በስምምነት ሊወስን ይችላል።

፫/ የሚመለሰው ንብረት ጥሬ ገንዘብ በሆነ ጊዜ ጠያቂው አገር የባንክ ማስተላለፊያ ዝርዝር ሁኔታዎችን ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል።

፬/ ንብረቱ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ በሆነ ጊዜ የንብረት መመለስ ሂደቱ ወይም የአወጋገድ ሂደቱ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል።

ክፍል ስምንት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፵፰. ለጠቋሚዎች የሚሰጥ ማበረታቻ

፩/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚመለስና የሚወረስ ንብረትን በሚመለከት ስለንብረቱ አመጣጥ እና የሚገኝበትን ሁኔታ በተመለከተ ጥቆማ በመሰጠቱና በጥቆማው መሠረት ንብረቱ የተወረሰ እንደሆነ ዝርዝር አፈፃፀሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የጠቋሚ ክፍያ የሚከፈል ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ጥቆማ የሚሰጥ ሰው ማንኛውም የንብረት ምርመራን የሚያደረግ፣ መረጃ የመሰብሰብ ወይም ክስ የማቅረብ ሥልጣን ያለውን ባለሙያ፣ ኃላፊን ወይም በሙያው አማካኝነት መረጃውን ያገኘ ማንኛውንም ሰው አያካትትም።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ከተካተቱት አካላት በተዘዋዋሪ የሰጠውን መረጃና ማስረጃ ይዞ ለሚቀርብ ሰው የጠቋሚ ክፍያ አይከፈለውም።

a) as per the bilateral agreement with the requesting state or based on international conventions;

b) in the absence of a bilateral agreement or international convention, based on case by case arrangements.

2/ If confiscation is directly or indirectly the result of coordinated law enforcement actions, the Ministry can enter in to an agreement for sharing the confiscated asset.

3/ When the asset to be returned is cash, the requesting country shall provide details of the bank account to the competent authority.

4/ When the asset is movable or immovable, the process of its return or disposal shall be in accordance with the laws of Ethiopia.

PART EIGHT

MISCELLANEOUS PROVISIONS

48. Reward for Whistleblowers

1/ Where a person has given information about the sources or the whereabouts of the asset recovered or confiscated based on this Proclamation, shall be entitled to a reward based on the Directives issued by the Ministry, if recovery is possible upon the information.

2/ A whistleblower that gives information as per Sub-Article (1) of this Article shall not include persons who are investigators, prosecutors, experts, managers, or any other person who accesses such information due to his professional engagement.

3/ An award shall not be given to anyone who gives information and evidence indirectly obtained from persons categorized under Sub-Article (2) of this Article.

፵፱. የሥራ ክፍል ስለማደራጀት

፩/ ሚኒስቴሩ በፌዴራል መንግስቱ ሥልጣን ስር የሚወድቅ የንብረት ማስመለስ ምርመራ የሚያደርግ፣ ክስ የሚመሰርት እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን የሚያከናውን የስራ ክፍል ያደራጃል፣ የስራ ክፍሉ ዐቃቤ ሕግ፣ መርማሪ እና ሌሎች አስፈላጊ ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች ይኖሩታል።

፪/ የስራ ክፍሉ በንብረት ማስመለስ ሂደት ውስጥ ተጠርጣሪን በመጥራት፣ በማቆየት፣ በብርበራ፣ በመያዝ፣ ንብረት በመውረስ፣ በማስተዳደር እና ሌሎች አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ከፖሊስ ተቋማት ጋር በመተባበር ይሠራል።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) በተደነገገው መሠረት የሚቀጠሩ መርማሪ እና ሌሎች አስፈላጊ ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች በዐቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚተዳደሩ ይሆናል።

፬/ ክልሎች በሥልጣናቸው ስር ከሚወድቁ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያከናውኑት የንብረት ማስመለስ ስራ በፍትህ ቢሮ ስር የራሳቸውን ተመሳሳይ የስራ ክፍል ያደራጃሉ።

፶. ተጎጅዎች የንብረት ማስመለስ ክስ ስለሚያቀርቡበት ሁኔታ

፩/ በወንጀል የተገኘው ንብረት የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የሌላ ግለሰብ ንብረት ከሆነ ይኸው ተቋም ወይም ግለሰብ በወንጀል የተገኘውን ንብረት እንዲመለስ በፍትሃ-ብሄር ክስ እንዲመሰርት ሚኒስቴሩ ፍቃድ ሊሰጥ ወይም ሊወክል ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ እነዚህ ተቋማት የሚመሰርቱትን ክስ በሚመለከት ውጤቱን ይከታተላል።

፶፩. የዳኝነት ሥልጣን

፩/ ለንብረት ማስመለስ ሂደቱ መነሻ የሆነው የተፈፀመው ወይም ተፈፅሟል ተብሎ የተጠረጠረውን ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የንብረት ማስመለስ ክሱንም በመጀመሪያ ደረጃ የመዳኘት ሥልጣን አለው።

49. Establishment of the Department

1/ The Ministry shall establish a department that comprises of prosecutors, investigators, and other experts with necessary special skills that are entrusted to asset recovery on matters falling within the Federal Jurisdiction

2/ The department works in cooperation with the police as per the Criminal Procedure Code to call upon suspects, detain, search, freeze, seize, confiscate, or manage assets or other necessary duties during the asset recovery process.

3/ Investigators and other experts with special skills employed under Sub-Article (1) of this Article shall be subjected to Public Prosecutors' Administration regulation.

4/ Regions shall establish their own similar division within their Justice Bureaus to conduct asset recovery under this Proclamation, on matters falling within their jurisdictions.

50. Conditions to File a Claim for Asset Recovery

1/ If the proceeds of a crime is the property of a government office, public enterprise or public organization or any individual. the appropriate organ may give its permission or delegate for organs or individual to initiate civil action against the suspected person for the recovery of the assets.

2/ The Ministery shall have the duty to follow up the result of such action by the other organs.

51. Court Jurisdiction

1/ The Court that has jurisdiction over the crime suspected or committed by the offender shall have first instance jurisdiction on the asset recovery.

፪/ ንብረቱ ከወንጀል ድርጊት ጋር ባለው ግንኙነት የተነሳ በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ የንብረት ማስመለስ ክስ በሚቀርብበት ጊዜ ለግንኙነቱ መነሻ የሆነውን ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የንብረት ማስመለስ ክሱንም በመጀመሪያ ደረጃ የመዳኘት ሥልጣን አለው።

2/ In the case of non-conviction based confiscation, the Court that has jurisdiction on the crime that causes non-conviction based confiscation shall have first instance jurisdiction on the asset recovery case.

፫/ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን በተመለከተ በፍትሃ-ብሔር ጉዳዮች የፍርድ ቤት ሥልጣን መሠረት ይዳኛል።

3/ The Court jurisdiction on unexplanied asset shall be determined based on laws governing civil matters.

፶፪. <u>የወንጀል ተጠያቂነት</u>

52. <u>Criminal Liability</u>

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም እንዲገልፅ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ ማስረጃውን እንዲያቀርብ ከመገደዱ በተጨማሪ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል።

1/ Any person who refuses to disclose or adduce any evidence requested as per the provisions of this Proclamation shall be punishable with imprisonment for a minimum of one year to a maximum of three years in addition to the order given to disclose the evidence.

፪/ ማስረጃ የተጠየቀው ሰው ማስረጃውን የደበቀ ፣ ሀሰተኛ ማስረጃ የሰጠ ፣ ማስረጃውን ያጠፋ ፣ መረጃ መጠየቁን ሚስጥራዊነት ያልጠበቀ እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

2/ Anyone who concealed, gives falsified evidence, destroys the evidence or violates confidentiality of the requested evidence shall be punishable with imprisonment for a minimum of three years to a maximum of five years.

፫/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በንብረቱ ላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን የእግድ፣ የመያዝ፣ የማስተዳደር ወይም የመውረስ ትዕዛዝ በመጣስ ትዕዛዙን የሚቃረን ማንኛውንም ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና በንብረቱ ላይ የደረሰ ጉዳት ወይም ያልተገባ ጥቅም በሚኖር ጊዜ በደረሰው ጉዳት ወይም በተገኘው ጥቅም ልክ ከ፲ በመቶ እስከ ፲፭ በመቶ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

3/ Any person who violates the order of freezing, seizure, confiscation or management issued by the Court pursuant to this Proclamation and commits an act contrary to the order, without prejudice to the penalty to pay fine from 10% to 15% of the extent to the damage caused or the advantage obtained, shall be punishable with simple imprisonment from one year to three years.

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሠረት ትዕዛዙ የተጣሰው የሕግ ሰውነት ባለው አካል በሆነ ጊዜ ከ ፳ በመቶ እስከ ፴ በመቶ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

4/ As per Sub-Article (3) of this Article, when the order is violated by a legal person, the fine shall be from 20% to 30%.

፶፫. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

53. <u>Power to Issue Regulation and Directive</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ለማውጣት ይችላል።

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

፪/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጣ ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፶፬. የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት

፩/ ከዚህ አዋጅ አፈፃፀም ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ እንደአግባብነቱ የፍትሃ-ብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎችን ብዜት በገንዘብ መደገፍን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፪ /፪ሺ፲ እና የሽብርተኛ ሀብት የሚታገድበት ሥነ-ሥርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺/፪ሺ፮ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

፶፭. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

፩/ ለንብረት ማስመለስ ዓላማ ሲባል በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ የንብረት ማስመለስ፣ ማገድ፣ መያዝ፣ ማስተዳደር እና መውረስን የሚመለከቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ የአዋጅ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሸረዋል፡-

ሀ) የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፬/፩ሺ፱፻፺፯፤

ለ) የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር ፶፻፹፪/፪ሺ፯፤

ሐ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፩፤

መ) የሽብር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፯/፪ሺ፲፪፤

ሠ) በሰው የመነገድና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፰/፪ሺ፲፪።

2/ The Ministry may issue Directive necessary for the implementation of this Proclamation or Regulation issued by the Council of Ministers.

54. Applicability of Other Laws

1/ Unless it contradicts with this Proclamation, the Civil Procedure Code and other appropriate Laws shall be applicable as necessary.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article this proclamation shall not affect the application of the Prevention and Suppression of Financing of the Proliferation of Weapons of Mass Destruction Proclamation No. 1132 /2019 and Procedure for Freezing of Terrorist Assets Council of Ministers Regulation No 306/2014.

55. Repealed and Inapplicable Laws

1/ For the purpose of asset recovery, the provision in the following Proclamations on asset recovery, freezing, seizure, asset management and confiscation are repealed:

a) The Revised Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence Proclamation No. 434/2005;

b) The Revised Anti-Corruption Special Procedure and Rules of Evidence (Amendment) Proclamation No.882/2015;

c) Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No. 780/2013;

d) Prevention, and Suppression of Terrorism Crime Proclamation No. 1176/2020;

e) Prevention and Suppression of Trafficking in Persons, Smuggling of Persons Proclamation No 1178/2020.

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ እና ልማዳዊ አሠራር ተፈፃሚ አይሆንም።

፶፮. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የውርስ አቤቱታ ቀርቦባቸው በሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮች በነበረው የሕግ ሥርዓት መሠረት የሚታዩ ይሆናል።

፶፯. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2/ Any Law or customary practice in contradiction with this Proclamation shall not be valid.

56. Transitional Provisions

Pending cases on asset recovery before the issuance of this Proclamation shall proceed in accordance with the preexisting laws.

57. Effective Date

This Proclamation shall enter in to force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, on this 2nd day of May, 2025

TAYE ATSKE SELASSIE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ